# ሻሞ! “274”

**የሽግግር መንግሥት ጥያቄ ለሀገራችን ወቅታዊ፣ ጠቃሚና፣ ምትክ የለሽ መሆኑን የሚያሳይ የቅድመ ምርጫ ግምትና ትንተና**




**ልደቱ አያሌው**

**ግንቦት፥ 2012 ዓ.ም.**

# 1. መግቢያ

የኮሮናቫይረስ ወደ ሀገራችን ከመግባቱ በፊት የዘንድሮ ምርጫ እንዲራዘምና፣ አንድ ሁሉን ዐቀፍ የሆነ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ስንጠይቅ እንደነበር ይታወቃል። በእኛ ጥረትና ትግል ሳይሆን በኮሮናቫይረስ አስገዳጅነት፣ ሀገራችን ምናልባትም ህልውናዋን ሊፈታተን ይችል ከነበረው ከምርጫ 2012 ግርግር ለጊዜውም ቢሆን አምልጣለች ማለት ይቻላል። የኮሮና ቫይረስ ወደ ሀገራችን መግባት፣ ምርጫውን እንዲራዘም ከማድረጉ በተጨማሪ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄያችንን የበለጠ አስፈላጊና ጥያቄውን ወደ ተግባር የመለወጡንም ዕድል ከቀድሞ በተሻለ ቀላል አድርጎታል። ይህንን የምንለውም በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች ነው።

**<u>የመጀመሪያዉ ምክንያት</u>፥** እንደሚታወቀው ቀደም ሲል ምርጫው እንዲራዘምና የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ስንጠይቅ የነበረው በዋናነት ሀገሪቷ ከምትገኝበት የፖለቲካ ውጥረት አኳያና "የለውጥ ሒደቱ" ስኬታማ ባልሆነበት ሁኔታ፣ የምናካሒደው ምርጫ በአንጻራዊነት ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ የመሆን ዕድል አይኖረውም በሚል ነው። እንዲያውም ሰላምና የሕግ የበላይነት ባልሰፈነበት ሁኔታ የምናካሒደው ምርጫ የሀገሪቷን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ውጤት ሊያስከትል ይችላል ከሚል ስጋትም ጭምር ነው። ይህ የቀደመ ስጋታችን አሁንም መቀጠሉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በኮሮናቫይረስ መከሰት ምክንያት ሀገራችን በአሁኑ ወቅት ከኅብረተሰብ የጤና ችግር በተጨማሪ በሐሳብ ለመገመት በማይቻል መጠን ለከፍተኛና ለተራዘመ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ተጋላጭ ሆናለች። ይህንን ከባድና ፈርጀ ብዙ የሆነ ሀገራዊ ችግር፣ እንኳንስ ከፋፋይ ወደሆነና የፖለቲካ ቀውስ ወደሚያስከትል ምርጫ ውስጥ ገብተን ቀርቶ፣ በሙሉ ትኩረትና ትብብር አንድ ላይ ቆመን ብንሠራም በቀላሉ ልንወጣው የምንችለው አይደለም። ስለዚህ በኮሮናቫይረስ መከሰት ምክንያት የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄያችን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ለሀገራችን የፖለቲካ ችግር አስፈላጊና ምትክ የለሽ መፍትሔ መሆኑ ግልጽ እየሆነ መጥቷል።

**<u>ሁለተኛው ምክንያት</u>፥** የምርጫውን መራዘምና የሽግግር መንግሥት መቋቋምን ቀደም ሲል ይቃወሙ የነበሩ አንዳንድ የፖለቲካ ኀይሎች ያቀርቡት የነበረው ብቸኛ መከራከሪያ "በሕገ መንግሥቱ የተቀመጠውን የምርጫ ጊዜ ማራዘም የሚቻልበት ዕድል የለም" የሚል እንደነበር ይታወሳል። ይህ የክርክር ነጥብ ከፖለቲካ አንጻር ቀድሞውንም ተገቢ ያልነበረ ቢሆንም፣ አሁን ግን በኮሮናቫይረስ መምጣት ምክንያት ክርክሩ እንዳይመለስ ሆኖ ተዘግቷል። ከእንግዲህ በአሁኑ ወቅት እየታየ እንዳለው ዐይን ባወጣ ድርቅና ካልሆነ በስተቀር የሕግ አንቀጽና ትርጓሜን ጠቅሶ "ምርጫውን ማራዘም አይቻልም" ብሎ መከራከር የሚቻልበት ዕድል የለም።

በዚህም ምክንያት፣ በአሁኑ ወቅት በሥልጣን ላይ የሚገኘው መንግሥት የሥልጣን ዘመኑ መስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም.ስለሚጠናቀቅና፣ የመንግሥትን የሥልጣን ዘመን ለአንድም ቀን ለማራዘም የሚያስችል ምንም ዓይነት ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ የሌለ በመሆኑ፣ ከመስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም. በኋላ ከመደበኛው የሕግ አሰራር ውጪ /Extra-Constitutional/ በሆነ የፖለቲካ ድርድር ሀገሪቷን እስከሚቀጥለው ምርጫ ድረስ ሊያስተዳድር የሚችል

አንድ ሁሉን ዐቀፍ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ከፊታችን ያለ ምትክ የሌለው አማራጭ ሆኗል። ***'ሀገሪቷ የአንድ ገዥ ፓርቲ የግል ንብረት ናት'*** ካልተባለ በስተቀርም፣ እንዲህ ዓይነቱ የፖለቲካ ውሳኔ ላይ ሊደረስ የሚገባው በገዥው ፓርቲ ውሳኔ ብቻ ሳይሆን ሁሉን ዐቀፍና አሳታፊ በሆነ ሀገራዊ የምክክር ሒደት /National Dialogue/ ነው። ስለሆነም የኮሮናቫይረስ መከሰት ምርጫውን ለማራዘም የነበረውን የሕግ እንቅፋት በማስወገድ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄን በቀላሉ የሚቻል አድርጎታል። ከእንግዲህ የሀገርን ጉዳይ ለማስቀደም፣ የሀገሪቷ የፖለቲካ ኀይሎች እንደተለመደው ቅንነትና የፖለቲካ ቁርጠኝነት ካላጣን በስተቀር፣ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄን ላለመቀበል ሰበብ ወይም እንቅፋት የሚሆን የሕግ ድንጋጌ የለም።

ነገር ግን፣ ብልጽግና ፓርቲ በአሁኑ ወቅት እያሳየው ካለው የሀገርን ጥቅም ከማስቀደም ይልቅ፣ ለራስ የፖለቲካ ሥልጣን የበለጠ ቀናዒ ከሆነውባህሪው አንጻር፣ በሕገ ወጥ መንገድ ሥልጣኑን ሊያራዝምና ምርጫውን ራሱ በፈለገው ጊዜና ሁኔታ እንዲካሔድ ሊወስን ይችላል። ገዥው ፓርቲም ወደዚህ ዓይነቱ ያልተገባ አቅጣጫ በመሄድ፣ (ምናልባትም የኮሮናቫይረስ ችግር በቀጣዩ ጥቂት ወራቶች ከተወገደ) ምርጫውን እስከ 2013 ዓ.ም. አጋማሽ ባለው ጊዜ ውስጥ የማካሔድ ፍላጎት እንዳለው ከውስጥ አዋቂ ምንጮች እየሰማን ነው። ይህ መረጃ እውነትነት ኖሮት ወደ ተግባር ከተለወጠ፥ ይህ የገዥው ፓርቲ ውሳኔ በሀገራችን ህልውና ላይ ከፍተኛ አደጋ የሚያስከትል ታሪካዊ ስህተት እና ክስተት ይሆናል። ምክንያቱም የሀገራችን የወቅቱ የፖለቲካ ችግር በእውነተኛ የውይይትና የድርድር ሒደት እንጂ፣ ከእንግዲህ ወዲያ በተለመደው ዓይነት የይስሙላ ምርጫ የሚፈታ አይደለም።ውጤታማ በሆነና መዋቅራዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት በሚያስችል የሽግግር ሒደት ባላለፍንበት ሁኔታ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ማካሔድም አይቻልም። የሆነ ሆኖ ገዥው ፓርቲ ወደዚህ ዓይነቱ የተሳሳተና ሕገ ወጥ ውሳኔ ሊገባ የሚችልበት ሰፊ ዕድል መኖሩን በመገንዘብና፣ ለሕዝብ ግንኙነት ተብለው በገዥው ፓርቲ በሚካሄዱ የታይታ ውይይቶች ሳይዘናጉ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁለት ፈርጅ ያለው ትግል ማካሔድ ይኖርባቸዋል።

**<u>የመጀመሪያው</u>**፥በሥልጣን ላይ የሚገኘው መንግሥት ከመስከረም 30 ቀን 2013 ዓ.ም. በኋላ በሕገ ወጥ መንገድ በሥልጣን ላይ እንዳይቀጥልና፣ ምርጫው የሚካሔድበትን ጊዜ ብቻውንናየራሱን መፃዒ ስልጣን በሚያረጋግጥ መንገድ እንዳይወስን የሚያደርግ **ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል** ማድረግ ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም፣ በተጭበረበረ ምርጫና በአፈና ድርጊት ለ29 ዓመታት በሥልጣን ላይ የቆየው ገዥው ፓርቲ ከእንግዲህ በሌላ ማናቸውም አሳማኝ ያልሆነ ሰበብና ምክንያት በሥልጣን ላይ እንዲቀጥል ሊፈቀድለት አይገባም። ገዢው ፓርቲ፣ በአሁኑ ወቅት ስልጣኑን በሀይል ለማስቀጠል እያሳየው ያለው አስፈሪ አዝማሚያ ከወዲሁ አደብ እንዲገዛ ካልተደረገ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደለየለት አምባገነናዊ እና ጨፍጫፊ ሃይል ሊቀየር እንደሚችል አጠራጣሪ አይሆንም፡፡ «ሳይቃጠል በቅጠል» እንዲሉ አደጋውን ከወዲሁ ለመቀልበስ መሞከር ለሀገሪቱ ህልውና እጅግ ጠቃሚ እና አስፈላጊ እርምጃ ይሆናል፡፡

በእንዲህ ዓይነቱ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ወደ ሀገራዊ ምርጫ የምንገባ ከሆነም፣ በምርጫው ግብጽን የመሰሉ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ካልሆኑ በስተቀር፣ የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ የትኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ኀይል አሸናፊ ወይም ተጠቃሚ ሊሆን እንደማይችል በመገንዘብ፣ እንዲህ ዓይነቱ ሀገራዊ አደጋ እንዳይከሰት ተቃዋሚው

ጎራ ሕዝቡን በማስተባበር ጠንካራ ትግል ማድረግ ይጠበቅበታል። ገዥው ፓርቲ ራሱን ከውይይትና ከድርድር ሒደት አርቆ ሥልጣኑን በጉልበት የማራዘሙን ድርጊት የሚገፋበት ከሆነ፣ ተቃዋሚ ጎራው በአንድ ላይ መቆም ከቻለና ይህንን የገዥውን ፓርቲ ሕገ ወጥነት ለሕዝቡ በበቂ መጠን ማሳመን ከቻለ፥ የተቃዋሚው ጎራ በራሱ ተነሳሽነትና መንገድ የሽግግር መንግሥት እስከ ማቋቋም የሚደርስ ትግል ማድረግ ይኖርበታል። ከመስከረም 30፣ 2013 በኋላ ከገዥው ፓርቲ የተለየ ግብዣና መፍትሔ መጠበቅ ሙሉ በሙሉ መቆም ይኖርበታል።

<u>**ሁለተኛው፥**</u> ተገቢውና ትክክለኛው መፍትሔ ከዚህ በላይ የተጠቀሰ ቢሆንም፣ መንግሥት በተለመደ አምባገነናዊ ባሕሪው በሕገ ወጥ መንገድ የራሱን ሥልጣን ማራዘም ከቻለና ምርጫው በአጭር ጊዜ እንዲካሔድ የሚወስን ከሆነ (የሚወስን ስለመሆኑ በእኔ በኩል ብዙም አልጠራጠርም)፣ ተቃዋሚው ጎራ በምርጫው ማግኘት የሚችለውን ከፍተኛ ውጤት አሟጦ ለማግኘት የሚያስችለውን ጥረትና ዝግጅት ከወዲሁ ማድረግ ይጠበቅበታል። ገዥው ፓርቲ የወቅቱን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሽፋን አድርጎና መንግሥታዊ መዋቅሩን ተጠቅሞ (ከላይ ለ6 ወራት ሥልጣኑን በማራዘም ዕቅዱ ላይ የሰማነውን ፍንጭ ታሳቢ በማድረግ) ውስጥ ውስጡን የራሱን የምርጫ ዝግጅት እያደረገ ነው። ተቃዋሚው ጎራ ይህንን ተገንዝቦ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በማይጻረር አግባብ የራሱን የምርጫ ዝግጅት ከወዲሁ ማድረግ ይኖርበታል። ይህንን ማድረግ ካልቻለና የኮሮና ችግር በተፈታ ማግስት ምርጫው እንዲካሔድ በገዥው ፓርቲ የሚወሰን ከሆነ ግን ተቃዋሚው ጎራ "ሥርገኛ መጣ" ዓይነት ችግር ውስጥ እንዳይገባ ከወዲሁ መዘጋጀት አለበት።

ከዚህ ግንዛቤ ጋር በተያያዘ፣ በአንድ በኩል አሁንም ምርጫው በቅርብ ጊዜ እንዲካሔድና የሽግግር መንግሥት የማቋቋሙ ጥያቄ ተቀባይነት እንዳያገኝ ለማድረግ እየጣሩ የሚገኙ የፖለቲካ ኀይሎች፣ ይህንን ለማድረግ ያስገደዳቸው ጠባብ የግልና የቡድን ፍላጎት ለሀገር ብቻ ሳይሆን ለራሳቸውም ፍላጎት የማይጠቅም መሆኑን ለማሳየት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከፍ ሲል ለመጥቀስ በተሞከረው ምክንያት ምርጫው በቅርብ ጊዜ መካሔዱ የማይቀር ከሆነ ተቃዋሚው ጎራ በሀገሪቷ ያለውን የፖለቲካ የኀይል አሰላለፍ በአግባቡ ተገንዝቦ የራሱን ቅድመ ዝግጅት ለማድረግ እንዲችል የቅድመ ምርጫ ውጤት ግምት ትንተና ከወዲሁ ማቅረብ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው ብዬ አምናለሁ። ቀደም ሲል ስለ «የሽግግር መንግሥት መቋቋም አስፈላጊነት» ባቀረብኩት ጽሑፍ ላይ እንደገለጽኩት፣ አሁን በምንገኝበት ነባራዊ የፖለቲካ ሁኔታ በአንጻራዊነት ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ የማካሔድ ዕድላችን አንድ አምስተኛ ወይም ከ20% ያነሰ ነው። ይህ ዕድል በኮሮናቫይረስ ወደ ሀገራችን መግባት ምክንያት የበለጠ ጠባብና ምናልባትም ወደ ዜሮ የተጠጋ ሆኗል። ይህ ግምት ከቅርቡ የዶ/ር ዐቢይ የከረረ የማስጠንቀቂያ ንግግርና መግለጫ በኋላ የበለጠ ተጠናክሯል።

ነገር ግን ምርጫው መካሔዱ የማይቀር ከሆነና በሆነ ተዐምራዊ ምክንያት በአንጻራዊነት ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ መሆን ቢችል፣ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ካለው የፖለቲካ የኀይል አሰላለፍ አኳያ ምርጫውን የትኛው የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ጎራ ሊያሸንፍ ይችላል? ለሚለው ጥያቄ «የቅድመ ምርጫ ውጤት ግምትና ትንተና» መስጠት ጠቃሚ ይሆናል። ጠቃሚነቱም በሚከተሉት አምስት ዋና ዋና ምክንያቶች ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

1. ምርጫው በቅርብ ጊዜ ከተካሔደ "እኛ የተሻለ የማሸነፍ ዕድል አለን" ብለው በማመን ምርጫው በቅርብ ጊዜ እንዲካሔድ ግፊት እያደረጉ የሚገኙ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅቶች የሠሩት ሒሳብ ምን ያህል ጥቅማቸውን የማያስጠብቅና ከእውነት የራቀ ግምት እንደሆነ ቆም ብለው ማሰብ እንዲችሉ፤
2. የቅድመ ምርጫ ግምቱንም ሆነ በአጠቃላይ በሀገሪቱ ያለውን የፖለቲካ የኀይል አሰላለፍ በአግባቡ መረዳትም፥ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ ዜጎች በተለያዩ ጉዳዮች ለሚይዟቸው አቋሞች እጅግ ጠቃሚ ግብዓት ሆነው ሊያገለግሉ የሚችሉ በመሆናቸው፤
3. ምርጫው የሚካሔድ ከሆነ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሀገሪቷ ያለውን የፖለቲካ የኀይል አሰላለፍ ሚዛን በአግባቡ ተገንዝበው በተናጠልም ሆነ በትብብር ማድረግ የሚገባቸውን ዝግጅት ከወዲሁ ለማድረግ እንዲችሉ፤
4. አንዳንድ ወገኖች እንደሚያስቡት መጪው ምርጫ በሆነ ተዐምራዊ ምክንያት ነጻና ፍትሐዊ ለመሆን ቢበቃ እንኳን፣ የምርጫው ውጤት በቀላሉ የሕዝብ መንግሥት ለማግኘት የሚያስችለን ሳይሆን፣ በእስካሁኑ የፖለቲካ ታሪካችን አይተነው የማናውቅና በበቂ ሁኔታ ያልተዘጋጀንበት አዲስ ዓይነት ውጤት ሊሆን እንደሚችል እንዲገነዘቡት ለማድረግ፤
5. እነዚህን ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ግንዛቤዎች በአግባቡ በመፍጠርም ሕዝቡ ከምርጫው በፊት ሀገራችን በቂ የዝግጅት ጊዜና የፖለቲካ ሒደት እንደሚያስፈልጋትና፣ ሁሉን ዐቀፍ የሆነ የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት ማቋቋምም ምን ያህል ወቅታዊ፣ አስፈላጊና፣ ሊታለፍ የማይገባው ጥያቄ እንደሆነ የሚኖረውን ግንዛቤ የበለጠ ለማጠናከር ነው።

በአጠቃላይም እንዲህ ዓይነቱን የምርጫ ውጤት ቅድመ ግምትና ትንተና ማቅረቤ፣ ሀገራችን በድኅረ ምርጫ 97 ወቅት የገጠማት ዓይነት ወይም ከዛ የባሰ የህልውና ቀውስ ውስጥ እንዳትገባ የማገዝ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል በሚል እምነት ነው።

በርግጥ፣ እንዲህ ዓይነቱን «የምርጫ ውጤት የቅድመ ግምትና ትንተና» ከፓርቲ ጥቅም አኳያ ካየነው ለአንድ ፓርቲ ውስጣዊ ሥራ እንጂ ለሕዝብ በይፋ መቅረብ የሚገባው አልነበረም። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ ግምገማ ከምርጫ ስትራቴጂ ዝግጅት አንጻር ሌሎች ፓርቲዎች ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት መረጃ ሆኖ ሊያገለግል ይችላልና። ነገር ግን ጉዳዩ ከሀገር ደኅንነት ጋር የተያያዘና እንዲህ ዓይነቱን የሕዝብ ጉዳይም በውስጠ ፓርቲ መዋቅር ብቻ ገድቦ መወያየቱ፣ ኋላ ላይ ምን ያህል ያልተፈለገ ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችል ከ97ቱ ምርጫ ከተገኘው ልምድ በመነሳት ይህንን ሰነድ በዚህ መልክ ለሕዝብ ውይይት ይፋ ማድረጉ በቀና አመለካከት ላይ የተመሠረተ ተመራጭ መንገድ ነው ብዬ አምናለሁ።

በዚህ ጽሑፍ ላይ የተገለጸውን የምርጫ ውጤት ግምት ለመስጠት የተሞከረውም፣ እንዲሁ ከአንድ ግለሰብ ወይም ፓርቲ አመለካከት ጋር ከተያያዘ ጠባብ ግምገማ በመነጨ አይደለም። ይህ ግምገማ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከተሰበሰበ ናሙና የመነጨ ባይሆንም፣ በአንዳንድ ክልሎች እስከ ወረዳ፣ በአንዳንድ ክልሎች ደግሞ ቢያንስ እስከ ዞን መዋቅር ድረስ ከሚገኙ የሀገሪቱ አካባቢዎችና ገዥውን ፓርቲ ጨምሮ፣ በሀገሪቱ ውስጥ የተለያየ አመለካከት

ካላቸው የፖለቲካ ድርጅት አመራሮችና አባላት መደበኛ ባልሆነ መንገድ የተሰበሰበ መረጃን መሠረት አድርጎ የቀረበ ግምትና ግምገማ ነው። ይህ የሆነውም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በፖለቲካ ዙሪያ የሚካሔድ ጥናት ግልጽና መደበኛ ከሆነ የጥናት አሠራር ይልቅ መደበኛ ባልሆነ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ቢሠራ የተሻለ ውጤታማ እንደሚሆን በማመን ነው። ይህ የቅድመ ምርጫ ውጤት ግምትና ትንተና የተሰጠውም አሁን የምንገኝበትን ተጨባጭ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ወደፊት እስከ ምርጫው ዕለት ድረስ በሚኖረው ጊዜ፣ በተለይም በመጨረሻዎቹ ሁለት ወራት የሚካሄዱ የምርጫ ዘመቻዎችና የምረጡኝ ክርክር መድረኮች ሊያመጡ የሚችሉትን ከፍተኛ የኀይል አሰላለፍ ለውጥ ጭምር ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

በመጨረሻም፥የ97 ምርጫን አስመልክቶ በወቅቱ በቅንጅት ውስጥ አቅርቤው የነበረው ተመሳሳይ «የቅድመ ምርጫ ውጤት ግምትና ትንተና» ኋላ ላይ በምርጫው ከመጣው ውጤት ብዙም ርቀት ያልነበረው እንደነበር እዚህ ላይ አስታውሶ ማለፉ ጠቃሚ ይሆናል።

## 2. ምርጫውን ማን ሊያሸንፍ ይችላል?

በምርጫ ሊመጣ የሚችለውን ውጤት፣ ወይም በምርጫው ማን አሸናፊ ሊሆን እንደሚችል ግምት ከመስጠቴ በፊት፣ የወቅቱ የሀገራችን የፖለቲካ የኀይል አሰላለፍ ምን እንደሚመስል ጠቅለል ባለ መልኩ ለማሳየት እሞክራለሁ። ከፖለቲካ አጀንዳ የኀይል አሰላለፍ አንጻር በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ያሉ ተፎካካሪ አስተሳሰቦች ወይም ቅራኔዎች በዋናነት ሁለት ናቸው። እነዚህ ሁለት አስተሳሰቦች በሌሎች ሀገራት እንደሚታየው ከፖለቲካና ከኢኮኖሚ ርዕዮተ ዓለም፣ ወይም ደግሞ ከሕዝቡ ተጨባጭ የዕለት ተዕለት ሕይወትና ኑሮ ጋር የተያያዙ አጀንዳዎች ሳይሆኑ፣ «**በዋናነት ከብሔር ተኮር እና ከሀገር አንድነት ተኮር አስተሳሰብ**» ወይንም በሌላ አገላለጽ «**ብሔር ተኮር ከሆነው የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት እና ሀገራዊ አደረጃጀት እንዳለ እንዲቀጥል ከመፈለግና ካለመፈለግ አስተሳሰብ**» ጋር በተያያዘ የሚንጸባረቁ ቅራኔዎች ናቸው።

ከአጀንዳ አንጻር ዋናዎቹ ተፎካካሪዎች እነዚህ ሁለት አስተሳሰቦች ቢሆኑም፣ ከፓርቲዎች የኀይል አሰላለፍ አንጻር ግን በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ሦስት ዋና ዋና የፖለቲካ ጎራዎች አሉ ማለት ይቻላል።

እነዚህም ጎራዎች፡-

1. ብሔር ተኮር የፖለቲካ ኀይሎች ጎራ (ኮንፌደራሊስት)
2. ሀገራዊ አንድነት ተኮር የፖለቲካ ኀይሎች ጎራ (ፌደራሊስት)
3. ብልጽግና ተኮር የፖለቲካ ኀይሎች ጎራ (አቋም አለመያዝን የመረጠ)፥ በማለት ልንከፍላቸው እንችላለን።

«እነዚህ ጎራዎች ስማቸውና ግብራቸው አብሮ ይሄዳል ወይ?» የሚለውን ጥያቄ፣ በተለይም «የብልጽግናው ጎራ በእውነትም የብልጽግና ኀይል ነው ወይ?» የሚለውን ጥያቄ ለጊዜው ወደ ጎን ትተን የኀይል አሰላለፉን በአግባቡ ለመገንዘብ እንዲረዳን ብቻ የጎራዎቹን ስያሜ በዚሁ መልክ እየተጠቀምንበት ብንቀጥል የተሻለ ይሆናል።

**"ብሔር ተኮር"** ባልነው ፈርጅ ውስጥ፥ በአብዛኛው ራሳቸውን በብሔር ስም ያደራጁና አነግን፣ ኦፌኮን፣ ህወሓትን፣ ኦብነግን የመሳሰሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ተካተውበት እናገኛለን። ነገር ግን አንዳንድ በደቡብ፣ በአፋር፣ በአማራና በትግራይ ክልል ወዘተ… በብሔር ስም ተደራጅተው ሳለ የኢትዮጵያን ህልውናና አንድነት ጥያቄ ውስጥ **የማያስገቡ** የፖለቲካ ድርጅቶችን ከብሔር ተኮር ይልቅ የአንድነት ጎራው ውስጥ ልንመድባቸው እንችላለን። ለምሳሌ አረናን፣ አብንን፣ አሕፓን፣ ጌሕዴድንና ቤጉዴግን የመሳሰሉትን ፓርቲዎች የአንድነት ተኮር ጎራው አካል አድርገን ልንቆጥራቸው እንችላለን።

**"አንድነት ተኮር"** ባልነው ጎራ ውስጥ ደግሞ አብዛኛዎቹ ራሳቸውን በኢትዮጵያዊነት ስም ያደራጁ ሕብረ-ብሔራዊ ፓርቲዎችንና ከፍ ሲል የጠቀስናቸው ዓይነት የኢትዮጵያን አንድነትና ህልውናን ጥያቄ ውስጥ **የማያስገቡ** በብሔር የተደራጁ ፓርቲዎች ጭምር ተካተው ይገኙበታል።

**"ብልጽግና ተኮር"**ባልነው ጎራ ውስጥ ደግሞ በዋናነት የሚካተተው የቀድሞው ኢሕአዴግ፣ ማለትም የአሁኑ ብልጽግና ፓርቲ ሲሆን፣ ነገር ግን በተቃዋሚ ፓርቲነት የተደራጁና በአቋም ደረጃ የብልጽግና ፓርቲ ደጋፊ የሆኑ፣ በዋናነት ኢዜማን የመሰሉ አንዳንድ ፓርቲዎች ጭምር ተካተው ይገኙበታል። ይህንን "የብልጽግና ተኮር" ጎራ ከሌሎቹ ሁለት ጎራዎች የተለየ የሚያደርገው በሀገሪቱ ካሉት ሁለት የፖለቲካ አስተሳሰብ ጎራዎች ውስጥ፣ ማለትም ከብሔር ተኮር ወይም ከአንድነት ተኮር አስተሳሰቦች ውስጥ ለየትኛው ታማኝ እንደሆነ የማይታወቅና፣ ሆን ብሎም እውነተኛ አቋሙን ለመደበቅ የሚፈልግ "አቋም የለሽ" ጎራ በመሆኑ ነው። ይህ ጎራ "አቋም የለሽ" ለመሆን የወሰደው አቋም ምን ዓይነት ዋጋ ሊያስከፍለው እንደሚችል ከዚህ በታች በተተነተነው  የምርጫ ውጤት ግምታችን ላይ የምናየው ይሆናል።

ብልጽግና ፓርቲ ከሀገሪቱ ሁለት መሠረታዊ የፖለቲካ ቅራኔዎች አንጻር በአሁኑ ወቅት ምንም ዓይነት ማኅበራዊ መሠረት የሌለው ፓርቲ ነው። አስተሳሰባዊ ቅራኔመሰረት ባደረገ የኀይል አሰላለፍ ደረጃም ቢሆን፣ እንደ አንድ የፖለቲካ ጎራ ሊቆጠር የሚችል አይደለም። እንደዚያም ሆኖ ግን የመንግሥትን መዋቅሮች የተቆጣጠረ፣ ሥራ ቀጣሪ የሆነ፣ ከፍተኛ ገንዘብ የሚያንቀሳቅስና ኪራይ አከፋፋይ መንግሥታዊ ኀይል /Incumbent/ ከመሆኑ አኳያ የግድ እንደ አንድ ተፎካካሪ ጎራ ሊታይ የሚገባው ኀይል ነው።

በሚመጣው ምርጫ ዋናው ፉክክር በእነዚህ ሦስት የፖለቲካ ጎራዎች መካከል ቢሆንም፣ ነገር ግን ሁሉም የሀገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በእነዚህ ሦስት ጎራዎች ገና ያልተሰባሰቡ በመሆኑ ምክንያት የመጪው ምርጫ ውጤት በእኛ እምነት ከዐሥር በማያንሱ ዋና ዋና ፓርቲዎች ወይም ጥምረቶች የሚከፋፈል ይሆናል። ሆኖም በ97ቱ ምርጫ ሲሆን እንደታየው፣ እነዚህ ፓርቲዎች ቢያንስ የምርጫው ዕለት ሲቃረብ ወይም ከምርጫው ውጤት መገለጽ በኋላ ያገኙትን የምርጫ ድምጽ **በሦስት ዋና ዋና ጎራዎች ለማጣመር የሚገደዱበትና የጥምር መንግሥት ለማቋቋም የሚሞከሩበት** ሁኔታ እንደሚፈጠር ታሳቢ በማድረግ የምርጫ ውጤት ግምታችንን በሦስቱ ጎራዎች አካተን ለማቅረብ እንሞክራለን።

ግምታችንን በቅድሚያ በክልሎች ደረጃ ጀምረን፣ በክልሎች ከሚኖረው የውጤት ግምት ድምር በመነሳት ደግሞ በፌደራል ደረጃ አሸናፊ ሊሆን የሚችለውን ጎራ ለመገመት እንሞክራለን። ለተሻለ አረዳድ ይረዳን ዘንድም ውጤቱን በቀላሉ ለመገመት ከምንችልባቸው ክልሎች ጀምረን፣ በቅደም ተከተል ለመገመት አስቸጋሪ የሆኑትን ክልሎች በማስከተል ለማየት እንሞክራለን።

## 2.1. ክልሎችን ማን ያሸንፋል?

### 2.1.1. ትግራይ ክልል (38 የምርጫ ወረዳ)

ከሁሉም ክልሎች በመጭው ምርጫ የሚመጣውን ውጤት ወደ ርግጠኝነት በተጠጋ መጠን አስቀድሞ መገመት የሚቻለው በትግራይ ክልል ይሆናል። በመጭው ምርጫ በትግራይ ክልል ዋናው (ምናልባትም ብቸኛው) የምርጫ አጀንዳ የትግራይ ክልል ሉዓላዊነትና የህወሓት ህልውና መቀጠል ጉዳይ ይሆናል። ይህንን አጀንዳ ከህወሓት በተሻለ መጠን በአሁኑ ወቅት ሊያሳካ የሚችል ድርጅት አለ ተብሎ በአብዛኛው የትግራይ ሕዝብ ዘንድ ስለማይታሰብ ህወሓት ምርጫውን 100% ሊያሸንፍ ይችላል።

ከትግራይ ሕዝብ ውስጥ ህወሓትን በተለያየ ምክንያት መምረጥ የማይፈልግ ከ10 እስከ 15% የሚደርስ ሕዝብ ሊኖር እንደሚችል መገመት ቢቻልም "የአብላጫ ድምጽ" በሚባለው የሀገራችን የምርጫ ሥርዓት ምክንያት የዚህ ሕዝብ ድምጽ ወደ መቀመጫ አሸናፊነት የሚቀየርበት ዕድል ግን አይኖርም። ማለትም ለምሳሌ በእያንዳንዱ የትግራይ ወረዳ ከ10 እስከ 15% የሆነው ብቻ ሳይሆን 49% የሆነው ሕዝብ የህወሓት ተቃዋሚ ሆኖ ቢገኝ እንኳ፣ ህወሓት በሀገራችን የምርጫ ሕግ መሠረት በ51% የየወረዳው የሕዝብ ድጋፍ ብቻ ምርጫውን 100% የማሸነፍ ዕድል ሊኖረው ይችላል። በሌላ አገላለጽም፣ የ49% ሕዝብ ድምጽ በአንድም ወንበር ሳይወከል ከንቱ ይቀራል ማለት ነው።

የሀገራችን ሕገ መንግሥት ተመጣጣኝ የውክልና ሥርዓትን ባገናዘበ ሁኔታ መሻሻል አለበት እያልን የምንጮኸው እንዲህ ዓይነቱ ኢፍትሐዊ አሠራር እንዲቀየር ስለምንፈልግ ጭምር ነው። ስለዚህ ከዚህ የምርጫ ውጤት ግምታችን አኳያ በዘንድሮው ምርጫ ህወሓት የክልሉን ምክር ቤት በአሸናፊነት ይዞ ይቀጥላል፤ ለፌደራሉ ፓርላማ ደግሞ 38 ወንበር ያሸንፋል። በነገራችን ላይ ከዚህ የእኛ ግምት በተቃራኒ አንዳንድ የብልጽግና ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች በመጭው ምርጫ ብልጽግና ፓርቲ ትግራይ ላይ እንደሚያሸንፍ በርግጠኝነት ሲናገሩ እየሰማን ነው። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱ ንግግር ብልጽግና ፓርቲ ምን ያህል የሀገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ ለመረዳት **በማያስችልና** በማይጨበጥ ቅዠት ውስጥ እንደሚገኝ ከማሳየት ያለፈ ትርጉም የለውም።

በአጠቃላይ በትግራይ ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ የምርጫ ውጤት፣ የመሃል ሀገር ፖለቲከኞች ህወሓትንና የትግራይን ሕዝብ በተመለከተ የምንጠቀምበት የፕሮፓጋንዳ ስልት ትርጉም ባለው መጠን እስካልተቀየረ ድረስ ወደፊትም የሚቀጥል ይሆናል። ይህ ሁኔታ ሲቀየር ግን የአንድነት ፖለቲካና አካባቢያዊ (አውራጃዊ) ስሜት ዋናው የትግራይ ብሔርተኞች ፈተና ይሆናል።

### 2.1.1.1. ኦሮሚያ ክልል (178 የምርጫ ወረዳ)

ከትግራይ ክልል ቀጥሎ የምርጫውን ውጤት ወደ ርግጠኝነት በሚጠጋ መጠን ለመገመት የሚቻለው በኦሮሚያ ክልል ነው። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት እየተሰማ ካለው መረጃ እንደምንገነዘበው ከዚህ ክልል ውስጥ በአነስተኛ ግምት 50 የሚሆኑት የምርጫ ወረዳዎች ላይ በጸጥታ ምክንያት ምርጫው ሊደረግ የሚችልበት ዕድል ስለሌለ የውጤት ግምታችን 128 የምርጫ ወረዳዎችን ብቻ መሠረት የሚያደርግ ይሆናል።

ቢያንስ በዘንድሮው ምርጫ በኦሮሚያ ክልል አብዛኛው ሕዝብ ድምጽ የሚሰጠው ለፖለቲካና ለኢኮኖሚ አጀንዳዎች ሳይሆን በዋናነት "ለነጻ አውጭነት ትግል" ውለታ መክፈያነት ይሆናል የሚል ጠንካራ ግምት አለ። በዚህ መመዘኛ መሠረት ላለፉት 40 ዓመታት "የነጻ አውጭነት" ትግል ያካሄደው ኦነግና ከኦነግ ጋር ተባብረው ወደ ምርጫው ለመግባት የወሰኑት እነ ኦፌኮ፣ ከ75% ያላነሰ መቀመጫ በማሸነፍ የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤትንና በፌደራሉ ፓርላማ 96 መቀመጫዎችን ሊያሸንፉ ይችላሉ። ቀሪውን 20% ወይም 26 መቀመጫዎች ደግሞ ብልጽግና ተኮር ጎራው፣ ቀሪውን 5% ወይም 6 መቀመጫዎች ደግሞ የአንድነት ተኮር ጎራው (በተለይም የሕዝብ ስብጥር ባላቸው ትልልቅ ከተሞችና አካባቢዎች) ሊያሸንፉ ይችላሉ። ብልጽግና ፓርቲ እስከ 20% የሚደርስ መቀመጫ ሊያሸንፍ የሚችለው በዋናነት በፓርቲው አመራርነት ያሉ አብዛኛዎቹ የኦሮሞ ተወላጆች ካላቸው አካባቢያዊ ማንነት ጋር በተያያዘ በሚወዳደሩባቸው ወረዳዎች ላይ ምርጫውን የማሸነፍ የተሻለ ዕድል ስለሚኖራቸው ነው። ብልጽግና ፓርቲ በአብዛኛዎቹ የኦሮሚያ ምርጫ ወረዳዎች በአማካይ ከ30 እስከ 40% የሚሆነውን የሕዝብ ድጋፍ ሊያገኝ የሚችል ፓርቲ ቢሆንም፣ ይህ ድጋፍ ግን በምርጫ ሥርዓቱ መሠረት በተሟላ ሁኔታ ወደ መቀመጫ አሸናፊነት የመቀየር ዕድል አይኖረውም።

### 2.1.2. ሶማሌ ክልል (24 የምርጫ ወረዳ)

እንደ ኦሮሚያ ክልል በሶማሌ ክልልም አብዛኛው ሕዝብ በመጪው ምርጫ ድምጽ የሚሰጠው "ለነጻ አውጭነት ትግል" ውለታ መክፈያነት ይሆናል የሚል ጠንካራ ግምት አለ። ስለሆነም ኦብነግ ከ60% ያላነሰ መቀመጫ በማሸነፍ የሱማሌ ክልል ምክር ቤትን የሚረከብ ሲሆን፣ ለፌደራሉ ፓርላማ ደግሞ 14 መቀመጫዎችን ሊያሸንፍ ይችላል። ቀሪውን 40% ወይንም 10 መቀመጫዎች ብልጽግና ፓርቲ ሊያሸንፍ ይችላል። ብልጽግና ፓርቲ ይህንን ያህል ለማሸነፍ የሚበቃውም፣ በክልሉ ውስጥ የጎሳ ወገንተኝነት የራሱ የማይናቅ ሚና ያለው በመሆኑ አንዳንድ ዕጩዎች የየትኛውም ፓርቲ አባል ሆነው ቢቀርቡ በጎሳ ማንነታቸው ብቻ ሊመረጡ የሚችሉበት ዕድል ያለ በመሆኑ ነው።

ከብልጽግና ፓርቲ በተጨማሪ በጣም ጥቂት መቀመጫዎችን ሊያሸንፉ የሚችሉ ጎሳ ተኮር ፓርቲዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህ ጎሳ ተኮር ፓርቲዎች አጠቃላይ ውጤቱን የሚያዛባ ሚና ሊኖራቸው ስለማይችል ከግምት ውጪ አድርገን ልናልፋቸው እችላለን። ከዚህ ምርጫ በኋላም የጎሳ ማንነትና የመገንጠል ጥያቄ የክልሉ ዋና ፈተናዎች ሆነው ሊቀጥሉ ይችላሉ።

### 2.1.3. አማራ ክልል (138 የምርጫ ወረዳ)

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ሦስት ክልሎች ቀጥሎ የምርጫውን ውጤት አስቀድሞ ለመገመት ቀለል የሚለው በአማራ ክልል እንደሆነ ቢገመትም፣ ከላይ ከተጠቀሱት ክልሎች በተለየ የአማራን ክልል ግምት ትንሽ የተወሳሰበ የሚያደርጉት ሦስት ምክንያቶች ይኖራሉ።

**<u>የመጀመሪያው ምክንያት</u>፥** ከሌሎች ክልሎች በተለየ በዚህ ክልል ሕዝቡ ድምጽ ሊሰጥ የሚችለው ለሦስት አጀንዳዎች ይሆናል። እነሱም፥ (1) ለአማራ ብሔርተኝነት መጠናከር፣ (2) ለኢትዮጵያ ህልውናና አንድነት ዋስትና ማግኘት፣ (3) የሕዝቡን ኑሮ ለሚመለከቱ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አጀንዳዎች ይሆናሉ።

**<u>ሁለተኛው ምክንያት</u>፥** ከሌሎች ክልሎች በተለየ በዚህ ክልል ለምርጫ የሚወዳደሩ ፓርቲዎች መሠረታዊ የዐላማ ልዩነት የሌላቸው ቢሆኑም በጋራ ተሰባስበው ለምርጫ የመወዳደር ድክመት ያለባቸው በመሆኑ ነው።

**<u>ሦስተኛው ምክንያት</u>፥** ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በፖለቲካ ልሒቃኑ ዙሪያ አካባቢያዊ (ክፍለ ሀገራዊ) ስሜቶች እያቆጠቆጡ በመምጣታቸው ነው።

ነገር ግን በአንድ በኩል ገዥው ብልጽግና ፓርቲ በክልሉ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነት ያጣበትና ደካማ የሆነበት ሁኔታ ላይ በመሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በክልሉ ውስጥ ብሔር ተኮር የሆኑ ሌሎች ተቀናቃኝ ኀይሎች የሌሉ በመሆኑ አብንን፣ አብሮነትንና መኢአድን የመሰሉ ፓርቲዎች ቢያንስ እርስ በርስ ላለመፎካከር መስማማት ከቻሉ የአንድነት ተኮር ጎራው በአነስተኛ ግምት ከ90% ያላነሰ መቀመጫ በማሸነፍ የአማራ ክልል ምክር ቤትንና ለፌደራሉ ፓርላማ 124 መቀመጫዎችን ሊያሸንፉ ይችላሉ። ከቀረው 10% ውስጥ ብልጽግና ፓርቲ 13 መቀመጫ፣ ብሔር ተኮር የሆነው ጎራ (ኦሮሚያ ልዩ ዞን) 1 መቀመጫ ሊያሸንፉ ይችላሉ።

ይህንን ውጤት ለማስጠበቅ ግን ቢያንስ አብንና አብሮነት እርስ በርስ ላለመፎካከር ሊስማሙ ይገባል። ምክንያቱም የክልሉ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት በአዲሱ የአማራ ብሔርተኝነትና በነባሩ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ለሁለት የተከፈለ አመለካከት ያለው በመሆኑ፣ በምርጫው የሕዝቡ ድምጽ በእነዚህ ሁለት አመለካከቶች እንዳይከፋፈል የሚያደርግ የፓርቲዎች ጥምረት መፍጠር የግድ ያስፈልጋል። ቢያንስ አብንና አብሮነት ወደዚህ ዓይነቱ ስምምነት መምጣት ከተሳናቸው የሚያገኙት ውጤት ከ90 ወደ 50% አካባቢ ዝቅ ሊል የሚችል ሲሆን፣ በአንጻሩ በክልሉ የሚገኙ አብዛኞቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እርስ በርስ ላለመፎካከር መስማማት ከቻሉ ደግሞ ውጤቱ ምናልባትም ከ90 ወደ 95% ሊያድግ ይችላል።

ብልጽግና ፓርቲ በአማራ ክልል እስከ 35% የሚደርስ የሕዝብ ድጋፍ ሊኖረው ይችላል። የአንድነት ኀይሉ ድምጽ እንዳይከፋፈል የሚያስችል ስምምነት ውስጥ እስከገባ ድረስ ግን ይህ የብልጽግና ፓርቲ ድጋፍ በሀገሪቱ የምርጫ ሥርዓት ምክንያት ወደ ወንበር አሸናፊነት የመቀየር ዕድል የለውም።

ነገር ግን የአንድነት ኀይሉ ለጋራ ጥቅም በአንድነት መቆም ያለመቻል አሳሳቢ ድክመት ያለበት በመሆኑ ውጤቱ እንዳይበላሽ ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥረት ማድረግ ይጠይቃል። ጉዳዩ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ በቅርቡ አብን ከአብሮነት ጋር ለመጣመር ባደረገው ጥረት የገጠመው ችግር በግልጽ አሳይቷል።

## 2.1.4. አዲስ አበባ ከተማ (23 የምርጫ ወረዳ)

አንዳንድ ሰዎች ኢቃለው እንደሚገምቱት ሳይሆን አዲስ አበባ ከተማ ከማንኛውም ክልል በላይ ብዙ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ለምርጫ የሚቀርቡበትና ከፍተኛ የድምጽ መከፋፈል የሚከሰትበት ከተማ ነው። በዚህም ምክንያት በየምርጫ ወረዳው ከ30 እስከ 40% ያልበለጠ የሕዝብ ድጋፍ ብቻ ያለው ኀይል ምርጫውን ሊያሸንፍ የሚችልበት ከተማ ነው። ከተማው የአንድነት ኀይሉ ዋና ማኀበራዊ መሠረት ሲሆን በዘንድሮው ምርጫ ሦስት ዋና ዋና አጀንዳዎች መፎካከሪያ ይሆናሉ።

የመጀመሪያውና ዋናው "አዲስ አበባ የማን ናት?" የሚለው ጥያቄ፣ ሁለተኛው የኢትዮጵያ ህልውናና አንድነት መቀጠል፣ ሦስተኛው ከሕዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር የተያያዙ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ጉዳዮች (በተለይም ሥራ አጥነትና የኑሮ ውድነት) ናቸው። በከተማዋ የመመረጥ ዕድል የሚኖረው ለእነዚህ ጥያቄዎች አስተማማኝ መልስ መስጠት የሚችል ኀይል ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪ በከተማው ከፍ ያለ ቁጥር ያለው ብሔር የምርጫውን ውጤት የመወሰን ከፍተኛ ሚና ሊኖረው ይችላል።

ከዚህ አንጻር፥ አብሮነት፣ አብንና ባልደራስን የመሳሰሉ ፓርቲዎች እርስ በርስ ላለመፎካከር ከተስማሙ የአንድነት ኀይሉ ከ80% ያላነሰ መቀመጫ በማሸነፍ የከተማዋን አስተዳደር ሊረከቡና 18 የፌደራል ፓርላማ መቀመጫ ሊያሸንፉ ይችላሉ። ቀሪው 20% ወይም 5 መቀመጫ ብልጽግና ፓርቲና የርሱ ደጋፊ የሆኑ ፓርቲዎች የማሸነፍ ዕድል ሊኖራቸው ይችላል። ብልጽግና ፓርቲና ኢዜማን የመሰሉ ፓርቲዎች በየወረዳው በድምር 25% የሚሆን የሕዝብ ድጋፍ ሊኖራቸው ቢችልም ይህ ድጋፍ በብዙዎቹ ወረዳዎች በምርጫ ሥርዓቱ ምክንያት ወደ ወንበር አሸናፊነት የሚቀየርበት ዕድል በጣም ጠባብ ነው። ይህንን ውጤት ለማስጠበቅም፥ ሲቻል አብዛኛዎቹ የአንድነት ኀይሎች፣ ቢያንስ ግን አብሮነትና አብን እርስ በርስ ላለመፎካከር አስቀድመው መስማማት የግድ ይኖርባቸዋል።

የብልጽግና ፓርቲ የገንዘብ ኀይል በአዲስ አበባ ቀላል የማይባል ተጽዕኖ ይኖረዋል። ነገር ግን ብልጽግና ፓርቲ ኦዴፓ በነበረበት ወቅት "አዲስ አበባ የኦሮሚያ ናት" በማለት የወሰነው ውሳኔና የአዲስ አበባን ሕዝብ ስብጥር ለመቀየር አደረገው የተባለው ሙከራ በምርጫው ሊደርስበት የሚችለውን ሽንፈት በማንኛውም ሌላ ምክንያት የማይቀለበስና አይቀሬ ያደርገዋል። የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች በአዲስ አበባ ከተማ ባለቤትነት ጉዳይ ላይ እያቀረቡት ያለው ጥያቄ እስከቀጠለ ድረስም፣ በአሁኑ ብቻ ሳይሆን በወደፊቶቹ ምርጫዎችም አሸናፊ የመሆን ዕድል አይኖራቸውም።

### 2.1.5. ደቡብ ክልል (123 የምርጫ ወረዳ)

ከሁሉም ክልሎች የምርጫውን ውጤት አስቀድሞ መገመት አስቸጋሪ የሚሆነው በደቡብ ክልል ነው። በሀገራችን ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ የሚካሔድ ከሆነ፣ በአሁኑም ሆነ ወደፊት ሊካሄዱ በሚችሉ ምርጫዎች እንደ አሜሪካው ፍሎሪዳ ግዛት፣ የሀገራችን የፓርቲዎች የጦር አውድማ /Battle Ground/ ወይንም ተወዛዋዥ ግዛት /Swing State/ ሊሆን የሚችለው ደቡብ ክልል ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት በአንድ በኩል፥ ደቡብ ክልል የተለያዩ ፍላጎቶች ያሉት ሕዝብና በርካታ ማንነትና ስብጥር የሚገኝበት ክልል በመሆኑ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፥ ክልሉ ከሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች በተለየ በሀገር አንድነትና በብሔሮች መብት መከበር መካከል ሚዛን የጠበቀ አመለካከት ያለበት ክልል በመሆኑ ነው።

በዘንድሮው ምርጫ በደቡብ ክልል ዋና ዋና የመፎካከሪያ ነጥብ የሚሆኑት አጀንዳዎች ሦስት ናቸው።

***<u>የመጀመሪያውና</u>*** ወቅታዊው፥ የዞኖች ክልል የመሆን ጥያቄ፤

***<u>ሁለተኛው፥</u>*** በኢትዮጵያ አንድነት መቀጠልና በብሔር ብሔረሰቦች መብት መከበር ዙሪያ ሚዛናዊ አቋም መኖር፤

***<u>ሦስተኛው፥</u>*** ከሕዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ፣በተለይም ከመሬት ጥበት እና ከወጣቶች ሥራ አጥነት ጋር የተያያዙ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ናቸው። ለእነዚህ ጉዳዮች አሳማኝ አማራጭ የሚያቀርብ ኀራ የመመረጥ ዕድሉ ሰፊ ይሆናል። ከሦስቱ የመፎካከሪያ አጀንዳዎች አንጻር ሲታይ አብዛኛው የደቡብ ክልል የአንድነት ተኮር ጎራው (የፌደራሊስት) ማኅበራዊ መሠረት ነው።

ከዚህ አንጻር፥ ሲቻል አብዛኛዎቹ የአንድነት ኀይሎች፣ ቢያንስ ግን አብሮነትና መድረክ (ኦፌኮን ሳይጨምር) እርስ በርስ ላለመፎካከር ተስማምተው ምርጫ ውስጥ ከገቡ በጣም ባነሰ ግምት 55% መቀመጫ አሸንፈው የክልሉን ምክር ቤት ሊረከቡና ለፌደራሉ ፓርላማ 68 መቀመጫዎችን ሊያሸንፉ ይችላሉ። ቀሪውን 30% ወይም 37 መቀመጫዎች የብልጽግና ጎራ፣ እንዲሁም 15% ወይም 18 መቀመጫ ብሔር ተኮር ጎራው ሊያሸንፍ ይችላል። ይህ ውጤት ዋስትና የሚኖረው ግን ቢያንስ መድረክ በተለይም የእነ ፕሮፌሰር በየነ ኢሶዴፓና አብሮነት እርስ በርስ ላለመፎካከር መስማማት ላይ ከደረሱ ነው። የመድረክ አባል የሆነውና ማኅበራዊ መሠረቱ ኦሮሚያ ብቻ የሆነው ኦፌኮ ከእነ ኦነግ ጋር አብሮ ለመሥራት ስምምነት በደረሰበት ሁኔታ የብሔር ተኮሩ ጎራ አካል እንጂ የአንድነት ተኮር ጎራው አካል ተደርጎ ሊታይ አይችልም።

ፕሮፌሰር መረራም በአጭር ጊዜ ውስጥ የአንድነት ጎራው አካል ተደርገው ከመታየት በአክራሪ የኦሮሞ ብሔርተኝነት ለመፈረጅ የበቁት በዚሁ ምክንያት ነው። ስለሆነም መድረክ በአጠቃላይም ሆነ፣ በተለይም ሕብረ ብሔራዊ አደረጃጀት የሚከተለው ኢሶዴፓ በዚህ ምርጫ ከኦፌኮ ጋር አብሮ በመቅረብ ጉዳት እንጂ ምንም ዓይነት ጥቅም ሊያገኝ አይችልም። መድረክም ሆነ ኢሶዴፓ በደቡብ ክልል የመመረጥ ዕድላቸውን ሊያሰፉ የሚችሉት

ራሳቸውን ከአፌኮ በግልጽ ነጥለው አብሮነትን ከመሰሉ ተመሳሳይ አጀንዳና አደረጃጀት ከሚከተሉ ፓርቲዎች ጋር እርስ በርስ ያለመፎካከር ስምምነት በመፍጠር ይሆናል። ምክንያቱም አብዛኛው የደቡብ ክልል የኦሮሞ ብሔርተኞችን ጽንፈኛ የፖለቲካ አካሔድ አብዝቶ የሚፈራ እንጂ የሚደገፍ አይደለም። ይህ ስሜት በክልሉ ከቀድሞ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የኦሮሞ ፖለቲከኞች በአዲስ አበባ ላይ እያነሱ ባሉት የባለቤትነት ጥያቄና ባለፉት ዐራት ዓመታት በርካታ የደቡብ ክልል ተወላጆች ከኦሮሚያ ክልል በግፍ በመባረራቸው ምክንያት የበለጠ ተጠናክሯል። ርግጥ ነው አንዳንድ በክልሉ ያሉ ፓርቲዎች ከአንዳንድ የኦሮሞ ድርጅቶች ጋር የተለየ ግንኙነት አላቸው። ብሔር ተኮር ጎራው የተወሰኑ መቀመጫዎች በዚህ ክልል የማሸነፍ ዕድል የሚኖረውም ለዚህ ነው።

እንዲያውም አብዛኛዎቹ የአንድነት ተኮር ኀይሎች እርስ በርስ ላለመፎካከር መስማማት ላይ መድረስ የሚችሉ ከሆነ የአንድነቱ ጎራ ውጤት ከ55% ወደ 70% የማደግ ዕድል ሊኖረው ይችላል። ከዚህ አንጻር መድረክ በተለይም ኢሶዴፓ የኀይል አሰላለፉን ለማስተካከል የሚወስደው አቋም የጨዋታውን ውጤት ቀያሪ /Game Changer/ ነው ማለት ይቻላል። ይህንን ውጤት በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስጠበቅ እንዲቻል ከኢሶዴፓ በተጨማሪም በየዞኑ ከሚገኙ የብሔር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመሥራት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

### 2.1.6. አናሳ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው ክልሎች (24 የምርጫ ወረዳዎች)

አናሳ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው ክልሎች ከአጠቃላይ ሀገሪቱ በድምር ከ5% ያልበለጡ የምርጫ ወረዳዎችን የሚሸፍኑ ናቸው። ማለትም፥ ቤኒሻንጉል ጉምዝ 9፣ አፋር 8፣ ጋምቤላ 3፣ ሐረሪ 2፣ ድሬዳዋ 2 የምርጫ ወረዳዎች አሏቸው። በእነዚህ ክልሎች ጎሳ ተኮር ፖለቲካ ቀላል የማይባል ተጽእኖ የሚኖረው ቢሆንም ከሌሎቹ ክልሎች በተለየ ከኢኮኖሚና ከመሠረተ ልማት ጋር የተያያዙ አጀንዳዎች በምርጫው ውጤት ላይ ተጽእኖ ይኖራቸዋል። በእነዚህ ክልሎች ሦስቱም ጎራዎች ከሞላ ጎደል ተመጣጣኝ የማሸነፍ ዕድል አላቸው።

ለምሳሌ ብልጽግና ፓርቲ በሁሉም ክልሎች ገዥ ፓርቲ በመሆኑ በእነዚህ ክልሎች ቀላል የማይባል መቀመጫ የማሸነፍ ዕድል ይኖረዋል። በርካታ መቀመጫ ባላቸው በአፋርና በቤኒሻንጉል ጉምዝ በዘንድሮው ምርጫ ጠንካራ ተፎካካሪ መሆን የሚችሉት አንዳንዶቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ደግሞ አደረጃጀታቸው ብሔር ተኮር ቢሆንም፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መቀጠል ቀና አመለካከት ያላቸው በመሆኑ ምክንያት እነዚህ ኀይሎች ከብሔር ተኮር ጎራው ይልቅ የአንድነት ተኮር ጎራውን ሊቀላቀሉ የሚችሉበት ዕድል ሊኖር ይችላል።

በእነዚህ ክልሎች የሚንቀሳቀሱት አብዛኛዎቹ ፓርቲዎች ብሔር ተኮር ከመሆናቸው አኳያ ደግሞ፣ የብሔር ተኮር ጎራውም የማይናቅ መቀመጫ የማግኘት ዕድል ሊኖረው ይችላል። ስለዚህ በእነዚህ ክልሎች ሦስቱ ጎራዎች፣ እያንዳንዳቸው በአማካይ ስምንት መቀመጫ ሊያሸንፉ የሚችሉበት ዕድል ሊኖር ይችላል። በዚህ ረገድ ሰፋ ያለ የግምት ስህተት ሊፈጠር ቢችል እንኳን እነዚህ ክልሎች አጠቃላይ ውክልናቸው ከ5% ያልበለጠ በመሆኑ አጠቃላዩን ሀገራዊ የውጤት ግምት የማዛባት አቅማቸው በጣም ዝቅተኛ ይሆናል።

## 3. ምርጫውን በክልልና በፌደራል ደረጃ ማን ሊያሸንፍ ይችላል?

ከዚህ በላይ ከተራ ቁጥር 2.1.1.እስከ 2.1.7. ድረስ በቀረበው ትንታኔ መሠረት በክልሎች ሦስቱ ጎራዎች በምርጫው ሊያገኙት የሚችሉት አማካይ የውጤት ግምት በሰንጠረዥ ሲቀመጥ የሚከተለውን ይመስላል። በአጠቃላይ የሀገሪቱ የምርጫ ወረዳዎች ቁጥር 547 ቢሆንም በጸጥታ ምክንያት በኦሮሚያ ክልል ምርጫ ሊካሔድ የማይችልባቸውን 50 የምርጫ ወረዳዎች ስንቀንስ፣ በሰንጠረዡ ላይ የሚኖረው የውጤት ግምት ስሌት 497 የምርጫ ወረዳዎችን ብቻ የሚመለከት ይሆናል።

**ሦስቱ የፖለቲካ ጎራዎች ሊያገኙ የሚችሉት ግምታዊ የምርጫ ውጤት**

| የምርጫ ክልል | በፌደራል ፓርላማ ያለው ክልላዊ የውክልና ወንበር ብዛት | 1. አንድነት ተኮር ጎራ (ፌደራሊስት) | | 2. ብልጽግና ተኮር ጎራ (አቋም አለመያዝን የመረጠ) | | 3. ብሔር ተኮር ጎራ (ኮንፌደራሊስት) | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በፌደራል ፓርላማ የሚያገኘው ክልላዊ ውክልና (በወንበር በቁጥር) | በፌደራል ፓርላማ የሚያገኘው ክልላዊ ውክልና (በመቶኛ/ ፐርሰንት) | በፌደራል ፓርላማ የሚያገኘው ክልላዊ ውክልና (በወንበር በቁጥር) | በፌደራል ፓርላማ የሚያገኘው ክልላዊ ውክልና (በመቶኛ/ ፐርሰንት) | በፌደራል ፓርላማ የሚያገኘው ክልላዊ ውክልና (በወንበር በቁጥር) | በፌደራል ፓርላማ የሚያገኘው ክልላዊ ውክልና (በመቶኛ/ ፐርሰንት) |
| ትግራይ | 38 | 0 | 0% | 0 | 0% | 38 | 100% |
| ኦሮሚያ | 128 | 6 | 5% | 26 | 20% | 96 | 75% |
| ሶማሌ | 24 | 0 | 0% | 10 | 40% | 14 | 60% |
| አማራ | 138 | 124 | 90% | 13 | 9% | 1 | 1% |
| ደቡብ | 123 | 68 | 55% | 37 | 30% | 18 | 15% |
| አዲስ አበባ | 23 | 18 | 80% | 5 | 20% | 0 | 0% |
| አናሳ ክልሎች | 24 | 8 | 33.30% | 8 | 33.30% | 8 | 33.30% |
| የፌደራል ፓርላማ (አጠቃላይ ውክልና) | 498 | 224 | 45% | 99 | 20% | 175 | 35% |

ከዚህ የውጤት ግምት እንደምንረዳው ግምቱ በተለያዩ ምክንያቶች ከፍና ዝቅ የማለት ዕድል ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የክልል ምክር ቤቶችን በማሸነፍ ረገድ የብልጽግና ተኮር ጎራ አናሳ ሕዝብ ከሚኖርባቸው ክልሎች መካከል የተወሰኑትን ሊያሸንፍ የሚችልበት ዕድል ያለ ቢሆንም ከትልልቆቹ ክልሎች ውስጥ ግን አንዱንም የማሸነፍ ግምት አልተሰጠውም። ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ብልጽግና ፓርቲ ሀገሪቱ ውስጥ ካሉ ሁለት የፖለቲካ የኀይል አሰላለፍ መገለጫ አመለካከቶች ውስጥ አንዱንም የማይወክል፣ ሁለቱንም የአስተሳሰብ ማኅበራዊ

መሠረቶች በእወደድ ባይነት ስልት /Populism/ ለማስደሰት ወይንም ላለማስከፋት ሲል በወሰደው “አቋም የለሽ” የመሆን ምርጫ ከሁለት ያጣ ወይንም ከማኅበራዊ መሠረቱ የተነቀለ የፖለቲካ ኀራ በመሆኑ ምክንያት ነው። ለዚህም ነው በአሁኑ ወቅትየነ ዶ/ር ዐቢይ አመራር፣ በብሄር ተኮር ኀራው፣ እንደ አሃዳዊው ሃይል፣ ለአንድነት ተኮር ኀራው ደግሞ እንደ ብሄርተኛ ሃይል ሲቆጠር የምናየው፡፡ይህ ማለት ግን ብልጽግና ፓርቲ አቋም የለሽ መሆንን ከእውቀት ማነስ የመረጠው ነው ማለት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በፖለቲካ አቋም የለሽ መሆን፥ ሆን ተብሎ የሚመረጥ የፖለቲካ ስልት ነው። ብልጽግና ፓርቲም በዚህ ወቅት ሥልጣኑን ማደላደል እስከሚችል ድረስ አቋም የለሽ መሆንን ተመራጭ ስልት አድርጎ ስለወሰደው ነው እንጂ፣ ባለማወቅ የያዘው አቋም አይደለም። ነገር ግን አሁን ባለው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኀይል አሰላለፍ አኳያ፣ እንዲህ ያለው ስልት ዋጋ የሚያስከፍል እንጂ የሚጠቅም አይደለም።

የእኛ ሀገር ምርጫ ከተጨባጭ የፖለቲካ አቋም ጋር ብዙም ግንኙነት የሌለው በመሆኑ ነው እንጂ፣ እንደ አቋም የለሽነቱ ቢሆን ኖሮ ብልጽግና ፓርቲ የዚህንም ያህል ግምት ማግኘት አልነበረበትም። ይህ ኀይል እንደቀድሞው ኢሕአዴግ የብሔር አደረጃጀቱንና ወገንተኝነቱን ለተወሰነ ጊዜ፣ ማለትም የብሔርተኝነት ስሜት በተወሰነ ደረጃ እስኪረግብ ድረስ በግልጽ አስጠብቆ ቢቀጥል ኖሮ፣ ወይም በማያሻማ ሁኔታ ዶ/ር ዐቢይ ወደ ሥልጣን እንደመጡ በፈጠሩት ስሜት መጠን የአንድነቱን ኀራ ተቀላቅሎ ቢሆን ኖሮ በሥልጣን ላይ ያለ መንግሥት በመሆን ሊገኙ የሚችሉት ጥቅሞች /Advantages/ ተጨምረውበት እስከ 51% የሚደርስ የሕዝብ ድጋፍ አግኝቶ ምርጫውን የማሸነፍ ዕድል ሊኖረው ይችል ነበር።

ይህ ባለመሆኑ በንጽጽር ሌሎቹ ሁለት ኀራዎች የተሻለ ውጤት እንዲያገኙ የሚያስችል ዕድል ተፈጥሯል። በነገራችን ላይ ብልጽግና ፓርቲ ገዥ ፓርቲና በሁሉም የሀገሪቷ የምርጫ ወረዳዎች እጩዎችን አቅርቦ መወዳደር የሚችል ፓርቲ ከመሆኑ አኳያ በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ የሚያገኘው የሕዝብ ድምጽ ቢደመር ከሦስቱም ኀራዎች የበለጠ ድርሻ ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን ከሀገሪቷ የምርጫ ሥርዓት ጋር በተያያዘ ይህ ድምጽ የብዛቱን ያህል ወደ ወንበር አሸናፊነት የመቀየር ዕድል አይኖረውም።

የብሔር ተኮር ኀራው በክልል ምክር ቤት ደረጃ፥ ትግራይን፣ ኦሮሚያን፣ ሶማሌ ክልልንና ከፊሎቹን አናሳ ሕዝብ የሚኖርባቸው ክልሎች የማሸነፍ ዕድል ይኖረዋል። ይህ ሊሆን የሚችለው በአብዛኞቹ የሀገሪቱ ክልሎች በዋናነት ብሔርተኝነት አሁንም ቀላል የማይባል ማኅበራዊ መሠረት ያለው በመሆኑ ነው። ከሁሉም በላይ ግን ለዚህ ኀይል የተሻለ የማሸነፍ ዕድል የፈጠረለት የቀድሞው ኢሕአዴግና (የአሁኑ ብልጽግና) አጋር ድርጅቶቹ ትክክለኛውን ጊዜ ባልጠበቀ ሁኔታ ከብሔር ማኅበራዊ መሠረታቸው በድንገት የመነቀል ርምጃ በመውሰዳቸው ምክንያት ነው ማለት ይቻላል። የኢሕአዴግና የአጋር ድርጅቶቹ ወደ ብልጽግና ፓርቲ የመቀየር ውሳኔ ለሀገሪቱ የወደፊት የፖለቲካ ሒደት እጅግ ጠቃሚ ርምጃ ቢሆንም ከመጪው የምርጫ ውጤት አኳያ ግን ውሳኔው ከማኅበራዊ መሠረት በድንገት የመነቀልና ለሌሎች ዕድልን አሳልፎ የመስጠት ውሳኔ ነው።

የአንድነት ተኮር ጎራው በክልል ምክር ቤት ደረጃ፥ አማራን፣ ደቡብንና አዲስ አበባ ከተማን የማሸነፍ ዕድል ይኖረዋል። ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት ቀድሞውንም እነዚህ ሦስት ክልሎች የአንድነት ተኮሩ ጎራ ማኅበራዊ መሠረት በመሆናቸው ነው፡፡ እነዚህ ክልሎች እየተካረረ በመጣው የብሔርተኝነት ስሜት ምክንያት በሀገሪቱ አንድነትና ህልውና ላይ ከፍተኛ ስጋት እያደረባቸው ስለመጣ፣ ቀድሞ ማኅበራዊ መሠረቱ ብሔርተኝነት የነበረው ብልጽግና ፓርቲና የብሔር ተኮር ጎራው የደጋፊዎቻቸውን ድምጽ በተወሰነ ደረጃ ስለሚከፋፍሉት ይሆናል። የብልጽግና ፓርቲ "አቋም የለሽ" የመሆን ምርጫና በጸጥታ ምክንያት በኦሮሚያ ክልል 50 የምርጫ ወረዳዎች ምርጫ የማይካሔድባቸው መሆኑም ለአንድነት ተኮር ጎራው ውጤት ማደግ የራሱ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ይህ ባይሆን ኖሮ የአንድነትና የብሔር ተኮር ጎራዉ በጣም ተቀራራቢ የሆነ ውጤት ሊኖራቸው ይችል ነበር።

ከዚህ አጠቃላይ የምርጫ ውጤት ቅድመ ግምት ለመረዳት እንደምንችለው ሦስቱ የፖለቲካ ጎራዎች በተናጠል የፌደራል መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችል ውጤት ሊያገኙ አይችሉም። ነገር ግን ከውጤት የቅደም ተከተል ደረጃ አንጻር የአንድነት ተኮር ጎራው 45% ወይንም 223 የፓርላማ መቀመጫ በማሸነፍ አንደኛ ደረጃን፤ የብሔር ተኮር ጎራው 35% ወይንም 175 የፓርላማ መቀመጫ በማሸነፍ ሁለተኛ ደረጃን፤ የብልጽግና ተኮር ጎራው 20% ወይም 99 የፓርላማ መቀመጫ በማሸነፍ ሦስተኛ ደረጃን ይይዛሉ።

ይህ ከሳይንሳዊ ጥናት ሳይሆን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከተሰበሰበ መረጃና ከፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታ ትንተና የመነጨ የምርጫ ውጤት ግምት፣ የስህተት ዕድሉ /Margin of Error/ ሰፋ ያለ እንደሚሆን ይገመታል። ነገር ግን በሦስቱ የፖለቲካ ጎራዎች መካከል ያለው የውጤት ግምት ልዩነት በጣም ሰፊ በመሆኑ ምክንያት በአጠቃላይ ግምቱ ላይ የሚፈጠሩ ስህተቶች አጠቃላይ የደረጃ ቅደም ተከተሉን የመለወጥ ዕድላቸው በጣም ጠባብ ይሆናል።

## 4. ቅድመ ግምቱን በመሠረታዊነት ሊያፋልሱ የሚችሉ ስጋቶች

ከዚህ የቅድሚያ ግምት ለመረዳት እንደምንችለው የአንድነት ተኮር ጎራው ከአንደኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ለመውረድ ከ49 መቀመጫዎች በላይ ማጣት አለበት። ወይም የብሔር ተኮር ጎራው ወደ አንደኛ ደረጃ ለመሸጋገር በተቃራኒው ከ49 በላይ መቀመጫዎችን ማግኘት አለበት።

የብልጽግና ተኮር ጎራው ከሦስተኛ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ለመሸጋገር ደግሞ ከ76 በላይ ተጨማሪ ወንበሮችን ማግኘት አለበት። ይህ የመሆኑ ዕድል ደግሞ በጣም ጠባብ ነው። ከዚህ አኳያ በተለይም ብልጽግና ፓርቲ በዚህ ምርጫ አንጋሽ /King Maker/ ከመሆን ያለፈ ሚና በቀላሉ ሊኖረው አይችልም።

ብልጽግና ፓርቲ ከሦስተኛ ደረጃነት ወደ አሸናፊነት ሊሸጋገር የሚችለው ዐይን ባወጣ መጠን ምርጫውን ማጭበርበርና አፈና መፈጸም ከቻለ ብቻ ነው። ነገር ግን በአሁኑ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የቱንም ያህል ፍላጎቱ ቢኖረውም ብልጽግና ፓርቲ በዚህ መጠን አፈና የመፈጸም አቅም የሌለው ደካማ ፓርቲ ከመሆኑም በላይ፣በእንዲህ ዓይነት አፈና ፈጽሞ ምርጫውን ካጭበረበረ በኋላ ራሱ ተረጋግቶ በሥልጣን ላይ ሊቀጥልም ሆነ ሀገሪቱ ሰላማዊና የተረጋጋች ሆና ልትቀጥል የምትችልበት ዕድል የለም። እንዲህ ዓይነት ግልጽ አፈና በምርጫ ሒደቱ ላይ የሚከሰት

ከሆነ ወዲያውኑ ወደ ቅድመ 2010 ነባራዊ ሁኔታ የመመለስና ወደለየለት የእርስ በርስ ጦርነት የመግባት ዕድላችን እጅግ ሰፊ ነው። ብልጽግና ፓርቲ በዋናነት የገንዘብ ኀይልንና የካድሬዎች ብዛትን በመተማመን ምርጫውን በአፈና የማሸነፍ ዕድል እንደሚኖረው ሊያስብ ቢችልም እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ግን በአንድ በኩል ከቀድሞው የኢሕአዴግ ሽንፈት ተገቢ ትምህርት ካለማግኘት ግብዝነት፣ በሌላ በኩል ደግሞ የወቅቱን የሀገሪቱን የፖለቲካ የኀይል አሰላለፍ በአግባቡ ለመረዳት ካለመቻል ግልብነት የሚመነጭ ከመሆን ያለፈ ትርጉም አይኖረውም።

የአንድነት ተኮር ጎራው የጥምር መንግሥት ለማቋቋም ከመገደድ ወጥቶ ብቻውን ከ274 መቀመጫዎች በላይ አሸንፎ መንግሥት ለማቋቋም ቢያንስ 50 ተጨማሪ መቀመጫዎች ማግኘት ይኖርበታል። እንዲህ ዓይነት ልዩነት ሊፈጥር የሚችል የስህተት ዕድል ሊኖር ስለማይችል ምርጫው ነጻና ፍትሐዊ እስከሆነ ድረስ የውጤቱን ደረጃ የሚቀይር አሳማኝ ምክንያት አይኖርም። በአጠቃላይ አንዱ ጎራ ብቻውን መንግሥት ለመመሥረት የሚችልበት ዕድል እንኳንስ በአሁኑ ምርጫና በሀገራችን፣ ወደፊትም በሚካሄዱት ሁለት ወይም ሦስት ምርጫዎች ይኖራል ብለን አንገምትም። ዴሞክራሲያዊ ባሕላችን ገና ባልጠነከረበትና ለእኛ ዓይነት ደሃ ሀገር የጠንካራ መንግሥት መኖር እጅግ አስፈላጊ ከመሆኑ አንጻርም እንዲህ ዓይነቱን የምርጫ ውጤት ወደፊት እንዴት ማስቀረት እንደምንችል በደንብ ማሰብ ይኖርብናል።

ከግምት ለውጥ አንጻር በአንድነት ጎራዉ ዙሪያ ሊኖር የሚችለው ዋና ስጋት፣ መድረክ ከአንድነት ኀይሉ ጋር እርስ በርስ ላለመሮካከር በቀላሉ ስምምነት ላይ ላይደርስ ይችላል የሚል ነው። ነገር ግን ይህ ስጋት እውን ቢሆንና በዚህ ምክንያት የአንድነት ተኮር ጎራው በደቡብ ክልል ግማሽ ያህሉን መቀመጫ ቢያጣ እንኳን፥ የሚያጣው የመቀመጫ መጠን 34 አካባቢ ስለሚሆን የአንደኛ ደረጃነቱን የማጣት ዕድል አይኖረውም። በብሔር ተኮር ጎራው ዙሪያ የሚኖረው ስጋት ደግሞ ብሔር ተኮር ጎራው ከህወሓት ጋር የመጣመሩ ዕድል በተለያየ ምክንያት ላይሳካ ይችላል የሚል ነው። ይህ ስጋት እውን መሆን ቢችልም የብሔር ተኮር ጎራው ሊያጣ የሚችለው የወንበር ብዛት 38 ብቻ ስለሚሆን የሁለተኛ ደረጃውን በቀላሉ ሊያጣ አይችልም።

ሌላው የብሔር ተኮር ጎራውን ውጤት ሊያሳድግ የሚችለው ዕድል በኦሮሚያ ክልል ያለው የሰላም ሁኔታ ተሻሽሎ በ50ዎቹ ወረዳዎች ምርጫው መካሔድ ከቻለ ነው። ይህ የመሆን ዕድሉ ጠባብ ቢሆንም ብሔር ተኮር ጎራው ሊያገኝ የሚችለው ተጨማሪ ወንበር ከአጠቃላይ ውጤቱ ምጣኔ አንጻር 38 አካባቢ ስለሚሆን በውጤት ደረጃው ላይ የሚያመጣው ለውጥ አይኖርም።

ስለዚህ ከዚህ አጠቃላይ ግምገማና ግምት በመነሳት ውጤቱ ከፍና ዝቅ የማለት ዕድል ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አጠቃላይ የምርጫው ውጤት ከዚህ ብዙም የተለየ አይሆንም የሚል የጠነከረ ግምት አለን። ነገር ግን የሀገራችን ፖለቲካ በፍጥነት ተለዋዋጭ ከመሆኑ፣ በውሳኔ አሰጣጥ ሒደት የግለሰቦች አሉታዊ ሚና ከፍተኛ ከመሆኑ፣ በምህዳሩ ውስጥ ያሉ ፓርቲዎች ቁጥር በጣም የበዛ ከመሆኑ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ አብዛኞዎቹ ፓርቲዎች በቂ የትግል ልምድ የሌላቸው ከመሆኑ አኳያ የምርጫን ውጤት ግምት ሊያከሽፍ የሚችል ምንም ዓይነት

ስጋት የለም ብሎ መደምደም አይቻልም። ይህንን ታሳቢ በማድረግ በሦስቱ ጎራዎች ዙሪያ ሊኖሩ የሚችሉትን መሠረታዊ ስጋቶች ጠቅለል አድርገን ለማየት እንሞክር።

**<u>ከብልጽግና ተኮር ጎራው ብንነሳ</u>፥**ይህ ጎራ ከዚህ ከፍ ሲል ከቀረበው የግምት ትንተና ብዙም የተለየ ውጤት ሊያመጣ የሚችልበት ዕድልም ሆነ ስጋት አለ ማለት አይቻልም። ይህ ጎራ ከአስተሳሰብ አንጻር እዚህ ግባ የሚባል ማኅበራዊ መሠረት የሌለውና በተወሰነ ደረጃ ከሕዝብ ሊያገኘው የሚችለው ድጋፍም መንግሥት ከመሆኑና ጥቅም አከፋፋይ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ከዚህ ግምት ብዙ በራቀ መጠን የተለየ ውጤት በመጪው ምርጫ ሊያገኝ አይችልም። ይልቁንም የዚህ ጎራ ውጤት ትርጉም ባለው መጠን ከፍ ወይም ዝቅ የማለት ዕድሉ የሚወሰነው ሌሎቹ ሁለቱ ጎራዎች በሚኖራቸው ድክመትና ጥንካሬ ይሆናል። በተጨማሪም ይህ ጎራ በአሁኑ ወቅት ማሳየት የጀመረውን የአምባገነንነት ባህሪ የበለጠ አጠናክሮ የሚቀጥልበት ከሆነ ሊያገኘው የሚችለው ውጤት የበለጠ ሊያሽቆለቁል ይችላል። ከሩቅ ጊዜ አኳያም ብልጽግና ፓርቲ በሀገሪቷ የፖለቲካ የኀይል አሰላለፍ ውስጥ የጠራ አመለካከትና አቋም ለመያዝ ካልወሰነ በስተቀር፣ እንዲያውም ከዚህ ምርጫ በኋላ እንደ አንድ የፖለቲካ ጎራ የመታየት ዕድልም ላይኖረው ይችላል። በዚህ ምክንያት ወደፊት በብልጽግና ፓርቲ ውስጥ ኢሕአዴግን ወይም ኢሕአዴግን መሰል ድርጅት እንደገና የመፍጠር እንቅስቃሴ ሲከሰት ልናይ እንችልም ይሆናል።

**<u>ወደ ብሔር ተኮር ጎራው ስንመጣ</u>፥**ይህ ጎራ በመጪው ምርጫ ከፍ ሲል ከቀረበው ግምት ብዙ የውጤት ለውጥ ይገጥመዋል ተብሎ ባይጠበቅም ውጤቱን ሊቀንሱ የሚችሉ ስጋቶች በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች ሊገጥሙት ይችላሉ።

**የመጀመሪያው፥**ብልጽግና ፓርቲን በዋናነት ተቆጣጥረው እየመሩት የሚገኙት ሰዎች የቀድሞው ኦሕዴድ አባላት ስለሆኑ እነዚህ ሰዎች አደረጃጀታቸውን ቢቀይሩም፣ በቀላሉ ከብሔርተኝነት አስተሳሰባቸው ሊላቀቁ ይችላሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም። በዚህ ምክንያት ዋናው የመጡበት ማኅበራዊ መሠረታቸው ኦሮሚያ ክልል በመሆኑ ይህንን ክልል የማስተዳደር ዕድል ላለማጣት ሲሉ ከፍተኛ ርብርብ ሊያደርጉና ከፍተኛ ገንዘብ ሊያፈሱ ይችላሉ። በዚህ ምክንያት የብሔር ተኮር ጎራው ከባድ ፈተና ሊገጥመው ይችላል።

**ሁለተኛ፥** ከዚህ የማኅበራዊ መሠረት ሽሚያ ጋር በተያያዘም ብልጽግና ፓርቲ በብዙ የኦሮሚያ አካባቢዎች ሽንፈት ይገጥመኛል ብሎ ከሰጋ የብሔር ተኮር ጎራውን ዕድል ለማጥበብ ሲል በዋናነት በኦሮሚያና በሱማሌ ክልል በፀጥታ ችግር ምክንያት ምርጫ ሊካሔድ የማይችልባቸውን ወረዳዎች ሆን ብሎ ሊያሰፋቸው ወይም ሊያበዛቸው ይችላል። በዚህ ምክንያትም የብሔር ተኮር ጎራው ተጨማሪ መቀመጫዎችን የማጣት አደጋ ሊገጥመው ይችላል።

ነገር ግን ይህ የምርጫ ውጤት ቅድመ ግምት በዋናነት ታሳቢ ያደረገው "ምርጫው በአንጻራዊነት ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ሆኖ ቢካሔድ" የሚለውን የቢሆን ግምት /Scenario/ በመሆኑ በዚህ ረገድ ሊፈጠሩ የሚችሉት ችግሮች የጎራውን የምርጫ ውጤት በጎላ ሁኔታ እንደማይቀይሩ አድርገን ልናልፈው እንችላለን። በዚህ ትንተና ላይ ከፍ ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው በአንድ በኩል ለኦሮሞ ሕዝብ "ነጻነት" ከ40 ዓመት በላይ የታገለው ኦነግ በዘንድሮው ምርጫ በትግል ታሪኩ ብቻ የመመረጥ ዕድሉ ሰፊ በመሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ አቶ ጃዋር መሐመድ በኦሮሞ

ሕዝብ ዘንድ በአሁኑ ወቅት ያለውን ከፍተኛ ተቀባይነት ተጠቅሞ ዋና ዋና የኦሮሞ ድርጅቶች በመጪው ምርጫ በአንድ ላይ ቆመው ወደ ምርጫ እንዲገቡ ማድረግ በመቻሉ ምክንያት በዚህ ምርጫ የተገመተውን ውጤት የማጣት አደጋ ብዙም አይኖረውም።

ይልቁንም ይህ ጎራ በሀገር ደረጃ የሚኖረው ሚና ከሩቅ ጊዜ አንጻር በሚከተሉት ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ማኅበራዊ መሠረቱ የመሟሸሽ አደጋ ሊገጥመው ይችላል።

***የመጀመሪያው፥***ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የዚህ ጎራ ዋና መሠረት በሆነው በኦሮሚያ ክልል የኦሮሞ ብሔርተኝነትን የሚገዳደሩ ሃይማኖታዊ፣ ሥነ ልቦናዊና በዋናነትም አካባቢያዊ ልዩነቶች የመከፋፈል አደጋ ይዘው መምጣታቸው አይቀሬ ይሆናል።

***ሁለተኛው፥***ሀገሪቷ በኢኮኖሚ ማደግ ከቻለች፣ ቴክኖሎጂና መሠረተ ልማት ይበልጥ እየተስፋፉ ከመጣ፣ አዲሱ ትውልድም ለዓለም ያለው እይታ እየሰፋና ጥያቄው እየተለወጠ ሲመጣ ንዑስ ብሔርተኝነት ቦታ እያጣ መምጣቱ አይቀሬ ይሆናል። ምክንያቱም የአንድን ሀገር አንድነት ከፖለቲካ ትርክት በላይ የሚያስተሳስረውና የሚያጸናው ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገትና የመሠረተ ልማት መስፋፋት በመሆኑ ነው። ይህ ዓይነቱ ለውጥ ግን በጥቂቱ የሁለት ዐሥርተ ዓመታት ሒደት ሊጠይቅ ይችላል።

***<u>ወደ አንድነት ተኮር ጎራው ስንመጣ</u>፥***ይህ ጎራ ከሌሎቹ ሁለት ጎራዎች በላይ የስጋት አደጋ ያዘለ ወይም የፈንጂ ወረዳ ነው ልንለው እንችላለን። ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደ ተሞከረው፥ የዚህ ጎራ ማኅበራዊ መሠረት አማራ ክልል፣ ደቡብ ክልልና አዲስ አበባ ከተማ ናቸው። ከስጋት አንጻር አማራ ክልልንና አዲስ አበባን በአንድ ፈርጅ፣ ደቡብ ክልልን ደግሞ በሌላ ሁለተኛ ፈርጅ ለይተን ልናየው እንችላለን። አማራ ክልልንና አዲስ አበባን ለማሸነፍ የአንድነት ኀይሉ በተለይም ደግሞ አብሮነትና አብን የግድ አብረው መቆም ይኖርባቸዋል። አብሮ መቆም በራሱ ግብ ስለሆነ ሳይሆን እነዚህ ፓርቲዎች አብረው ባለመቆማቸው ራሳቸውንና ሕዝቡን ውጤት የሚያሳጡበት፣ ለሌላው ተቀናቃኝ ጎራ ደግሞ ያልተገባ ዕድል የሚፈጥሩበት አደጋ ስለሚኖር ነው። ይህ አደጋ በሦስት ምክንያት ሊፈጠር ይችላል።

***የመጀመሪያው አደጋ፥***በዚህ ጎራ ዙሪያ ያሉ አንዳንድ የፖለቲካ አመራሮች ከቆሙለት ዐላማና ሕዝብ ጥቅም በላይ ለግል ሥልጣን፣ ስሜትና ዝና የማዘንበል ድክመት ስላለባቸው ነው። ይህ ድክመት ባለፈው 28 ዓመት የፖለቲካ ሒደት ሀገሪቷን ብዙ ዋጋ ያስከፈለ ሲሆን በቅርቡ አብሮነት፣ አብን፣ ባልደራስና መኢአድ ሊፈጥሩት አስበውት በነበረው ኅብረት መክሸፍም በግልጽ ታይቷል። ይህ አብሮ የመሥራት ጥረት ለጎራውም ሆነ ለሕዝቡ ትግል ውጤታማነት ያለው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ እየታወቀ፣ አንዳንድ ግለሰቦች ከአንድ ግለሰብ ጋር አብረው ላለመሥራት ስለፈለጉ ብቻ የተፈጠረ ችግር ነው። እንዲህ ዓይነቱ ችግር ወደፊትም ሊቀጥል ከቻለ የአንድነቱ ጎራ ከላይ የተሰጠውን ግምት የማያሳካበት አደጋ ሊኖር ይችላል።

***ሁለተኛው አደጋ፥***አብን እስካሁን ምርጫ ተሳትፎ የማያውቅና ለፖለቲካ ትግሉም አዲስ ፓርቲ ከመሆኑ አኳያ፣ በአንድ በኩል በእጁ ላይ ምን ያህል ከባድ ሀገራዊ ኀላፊነትና ዕድል እንዳለ በውል ካለመረዳት፣ በሌላ በኩል

ደግሞ ስለራሱና በምርጫው ስለሚያገኘው ውጤት ሊኖረው ከሚችለው የተሳሳተ ወይም የተጋነነ ግምት የሚመነጭ ሊሆን ይችላል። ማለትም ላለፉት ዐራት ዓመታት የተፈጠረውን አዲስ የአማራ ብሔርተኝነት የሁሉም አማራ ሕዝብ ስሜትና የማይለወጥ ክስተት አድርጎ በመቁጠር ሌሎች ኅብረ ብሔራዊ ፓርቲዎች በምርጫው የሚኖራቸውን ሚና አሳንሶ የማየትና ብቻችንን በምርጫ ብንሳተፍ ለትልቅ ውጤት እንበቃለን የሚል የተሳሳተ ግምት ሊኖር ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ በኃላ ሁኔታ የሚኖር ከሆነ በሚመጣው ምርጫ አብንን፣ አንድነት ጎራውንና በአጠቃላይም ሀገሪቷን የሚያስከፍለው ዋጋ ከፍተኛ ይሆናል። ስህተቱም ታሪካዊ ስህተት ይሆናል።

አብን በመጭው ምርጫ የሚኖረው ሚና እጅግ ከፍተኛና ምትክ የለሽ ሆኖ እያለ፣ ብቻውን ወደ ምርጫ የሚገባ ከሆነ ግን እንኳንስ በሌሎች ክልሎችና የአማራ ክልል ምክር ቤትንም ለማሸነፍ የሚኖረው ዕድል ጠባብ ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መረዳት ይኖርበታል። የዚህ መጣጥፍ ስፋት ስለማይመጥን እንጂ ይህንን ለምን ማለት እንደሚቻል ብዙ አሳማኝ ምክንያቶችን አቅርቦ ማስረዳት ይቻላል። በነገራችን ላይ በ97 ምርጫ ወቅትም ራሱን እንደ ብቸኛ የአማራ ሕዝብ ወኪል ይቆጥር የነበረው መኢአድ "በአዲስ አበባና በአማራ ክልል ከእኔ የተሻለ አሸናፊ የሚሆን የለም" የሚል የተሳሳተ ግምት ነበረው። ነገር ግን በሒደት የምርጫው ውጤት ሲታይ ኢዴፓ በአዲስ አበባም ሆነ በአማራ ክልል ከመኢአድ የበለጠ ተቀባይነት እንዳለው በተጨባጭ ታይቷል።

ዶ/ር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ሲመጡና የኢትዮጵያዊነት አጀንዳን ማቀንቀን ሲጀምሩም ከየትኛውም ክልል በላይ ተቀባይነት ያገኙት በአማራ ክልል ነበር ማለት ይቻላል። እንደዛሬው ሳይሆን፣ ዶ/ር ዐቢይ ወደ ሥልጣን እንደመጡ በሀገራችን ምርጫ ቢካሔድ ኖሮ፣ የአማራው ሕዝብ ስለ ዶ/ር ዐቢይ ኦሮሞነትም ሆነ ኢሕአዴግነት ምንም ማሰብ ሳያስፈልገው ቁጥር አንድ ተመራጭ ሊያደርጋቸው ይችል ነበር። ከዚህ የምንማረው የኢትዮጵያዊነት አጀንዳ በአማራው ሕዝብ ውስጥ ምን ያህል በቀላሉ በኖ የማይጠፋ ጠንካራ መሠረት ያለው ማንነት መሆኑን ነው። በተለይም ለአማራ ብሔርተኝነት መጠናከር ዋና ምክንያት የነበረው የህወሓት የበላይነትና ተጽዕኖ በተወገደበት በአሁኑ ወቅት የአማራ ብሔርተኝነት ከሁለት ዓመት በፊት ሲሆን እንደታየው ዋና ገዥ አስተሳሰብ ሆኖ የመቀጠል ዕድሉ ዝቅተኛ ነው።

**ሦስተኛው አደጋ ሊመጣ የሚችለው፥** ከብልጽግና ጎራው አቅጣጫ ይሆናል። የቀድሞው ኢዴፓ ወይም የአማራ ብልጽግና ፓርቲ እጅግ የተዳከመና በሕዝቡ ውስጥ ትርጉም ያለው ሥራ መሥራት የማይችል ቢሆንም የአማራ ክልልን የማስተዳደር ሚናውን ላለማጣት ሲል አብንን ለመከፋፈል፣ ለማዳከምና ለማፍረስ ከፍተኛ ጥረት ሊያደርግ ይችላል። ለዚህ ደግሞ የአብን ልምድ ማጣትና አሁን አሁን በክልሉ ማቆጥቆጥ የጀመረው "ክፍለ ሀገራዊ" ስሜት ይህ እንዲሆን ዕድል ይፈጥራል። አብን በአንድ በኩል ይህንን ከገዥው ፓርቲ ሊመጣ የሚችልን ጥቃት በአግባቡ ተገንዝቦ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከአማራም ሆነ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም አኳያ በእጁ ላይ ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነት የሚገኝ መሆኑን ተገንዝቦ ህልውናውን ለማስጠበቅ የሚያበቃ የአመራር ብቃት ካላሳየ በስተቀር የመፍረስ አደጋ ሊገጥመውና በዚህ ግምት ላይ የተቀመጠው የምርጫ ውጤትም ሊፋለስ ይችላል። ይህ አደጋ ለአማራ ሕዝብም ሆነ በአጠቃላይ ሀገሪቱ ላይ የሚያስከትለውን አደገኛ ውጤት በውል በመገንዘብ አብን በከፍተኛ ጥንካሬ፣

ጥንቃቄና ብልሃት መራመድ ይጠበቅበታል። ሆኖም በአብን ህልውና ላይ ሊከሰት የሚችለው አደጋ በአጠቃላይም የአንድነት ኀይሉ ላይ ሊከሰት የሚችል አደጋ መሆኑን በመገንዘብ አደጋውን እንዲቋቋመው ሁሉም የአንድነት ኀይል አብንን ሊያግዘው ይገባል።

ደቡብ ክልልን ከማሸነፍ አንጻርም በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ሲቻል ሁሉም የአንድነት ኀይሎች፣ ቢያንስ ግን አብሮነትና መድረክ (ከኦፌኮ ውጪ) የግድ አብረው ወደ ምርጫ መግባት አለባቸው። በዚህ ረገድ የፖለቲካ መሪዎች በግለኝነት ሊፈጥሩት የሚችሉት ችግር መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋናው ስጋት ግን «እነ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ለረዥም ዓመታት አብረዋቸው ሲሰሩ ከቆዩት ከእነ ፕሮፌሰር መረራ ተነጥለው ከአንድነት ኀይሉ ጋር አብረው ለመሥራት ምን ያህል በቀላሉ ሊወስኑ ይችላሉ?» በሚለው ጥያቄ የሚወሰን ይሆናል። ነገር ግን ጉዳዩ የማኀበራዊ ግንኙነት ጉዳይ ሳይሆን የፖለቲካ ጥቅም ጉዳይ ስለሆነ፣ አሁን በሀገሪቷ ካለው የፖለቲካ የኀይል አሰላለፍ አንጻር እነ ፕሮፌሰር በየነ ለራሳቸውና እንወክለዋለን ለሚሉት ሕዝብ ጥቅም ሲሉ ወደዚህ ውሳኔ ሊመጡ ይችላሉ ብሎ መገመት ይቻላል።

ከእነዚህ ስጋቶች ጋር በተያያዘ ሌላው ግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባውና ለአንድነት ጎራው ተባብሮ መሥራት እንቅፋት ሊሆን የሚችለው አንዱ ችግር የእኔ የዚህ ፅሑፍ ፀሐፊ "ስም" ነው። በቅርቡ ከአብን ጋር አብሮ ለመሥራት ከተደረገው ሙከራ መክሸፍ ጋርም ሆነ ከ97ቱ ምርጫ ሒደት ለመገንዘብ እንደሚቻለው በርካታ ሰዎች ከእኔ ጋር አብሮ ለመሥራት የማያስችል የፖለቲካ ዐይነ ጥላ አለባቸው። በ97ቱ ምርጫ እንደ ሆነው ሁሉ ይህ ችግር በመጪው ምርጫም ችግር ሆኖ መቀጠል ስለሌለበትና በአንድ ግለሰብ ምክንያትም ይህ ትልቅ የሕዝብና የሀገር ጉዳይ መሰናከል ስለማይገባው፣ የምርጫው ጊዜ ከመቃረቡ በፊት በእኔ በኩል ለችግሩ መፍትሔ ለማግኘት የሚረዳ ርምጃ በራሴ ላይ ለመውሰድ እገደዳለሁ፡፡ የ97ቱ አሳዛኝ ሁኔታ በራሴም ላይ ሆነ በትግል ሒደቱ ላይ ዳግም ሲከሰት ለማየት ፍላጎቱም ሆነ አቅሙ የለኝምና።

ይህንን መፍትሔና የምርጫውን መራዘም እንደ አንድ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀምም የአንድነት ጎራው አብሮ የመሥራቱን ጥረት እንደገና በአስቸኳይ መቀጠል ይኖርበታል። የአንድነት ኀይሉ አብሮ የመሥራት ጉዳይን የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን በምንም ዓይነት ምክንያት በፍጹም ሊስተጓጎል የማይገባው ትልቅ ሀገራዊ ተልዕኮ አድርጎ ማየት ይኖርበታል። የግለሰብና የቡድን ጥቅም ጉዳይ ለሀገርና ለሕዝብ ዘለቄታዊ ጥቅም ሲባል ወደ ጎን መገፋት አለበት። ለዚህም ከ97ቱ ስህተት ተገቢ ትምህርት መቅሰማችንን ሁላችንም በተግባር ማሳየት ይኖርብናል። የአንድነት ጎራው ይህንን ማድረግ የማይችል ከሆነ ግን እንኳንስ በፌደራል መንግሥት ደረጃ ዋና ተፎካካሪ ሊሆንና፥ አዲስ አበባን፣ ደቡብንና አማራ ክልልንም ብቻውን ማሸነፍ የማይችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

# 5. ማጠቃለያ

የመጪው ምርጫ በሆነ ተዐምራዊ ምክንያት በአንጻራዊነት ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ሆኖ ከተጠናቀቀ የተለያዩ ክልሎች በተለያዩ የፖለቲካ ኀራዎች አሸናፊነት የሚያዙ ሲሆን፣ ማዕከላዊ መንግሥቱን አንድ የፖለቲካ ኀራ ብቻውን የሚያሸንፍበት ዕድል ስለማይኖር የጥምር መንግሥት የማቋቋም ጉዳይ ግዴታ ይሆናል። ከፍ ሲል ከቀረበው የውጤት ግምት አንጻር የጥምር መንግሥት ለማቋቋም ቀዳሚ ድርሻ የሚኖረው የአንድነት ተኮር ኀራው ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው የብሔር ተኮር ኀራውም ከብልጽግና ተኮር ኀራው ጋር መስማማት ከቻለም ዕድሉን ከአንድነት ኀራው ቀምቶ ጥምር መንግሥት የማቋቋም የጠበበ ዕድል ይኖረዋል። የጠበበ ዕድል የምንለው ያለምክንያት ሳይሆን የሁለቱ ኀራ የወንበር ቁጥር ሲደመር የሚመጣው ውጤት መንግሥት ለመመስረት የሚያበቃው የመጨረሻ ዝቅተኛው የመቀመጫ ብዛት፥ ማለትም **274** በመሆኑ ነው። ይህ የሚያሳየን የአንድነት ኀራው በመጪው ምርጫ የሚኖረውን ውጤት ለማበላሸትም ሆነ የበለጠ የሰመረ እንዲሆን ለማድረግ አንድ ወይም ጥቂት ወንበሮች ምን ያህል ወሳኝ መሆናቸውን ነው።

ከዚህ የምንረዳው ሌላው ቁም ነገር፥ የብሔር ተኮር ወይም የብልጽግና ኀራው ውጤት እዚህ ላይ ከተሰጠው ግምት በሆነ ምክንያት የሚያንስ ከሆነ ሁለቱ ኀራዎች ተጣምረው መንግሥት ለማቋቋም የማይችሉበት ዕድልም መኖሩን ነው። ይህም ማለት የአንድነት ተኮር ኀራውና የብሔር ተኮር ኀራው አጀንዳቸውን አቻችለው መጣመር ካልቻሉ፣ ወይም በሆነ ተዐምር ሦስቱም ኀራዎች አንድ የጥምር መንግሥት ማቋቋም ካልቻሉ በስተቀር በሀገሪቱ ጭራሹኑ መንግሥት ለማቋቋም የማይቻልበትም ሁኔታ ሊኖር ይችላል ማለት ነው።

በአጠቃላይ ምርጫው ውጤታማ በሆነ የሽግግር ሒደት ከማለፋችን በፊት በቅርብ ጊዜ የሚካሔድ ከሆነ በድኅረ ምርጫው ወቅት የሚከሰተውን ሁኔታ በርግጠኝነት መገመት አስቸጋሪ ነው። ከቀረበው ግምት ለመረዳት እንደምንችለው ከምርጫው በኋላ መንግሥት ለማቋቋም ከሦስቱ ኀራዎች ውስጥ ሁለቱ የግድ መስማማት አለባቸው። አንደኛው ኀራ ከየትኛው ኀራ ጋር መጣመር እንደሚመርጥ አስቀድሞ ስለማይታወቅ ሦስቱም ኀራዎች ያገኙት የድምጽ መጠን ምንም ይሁን ምን ጥምር መንግሥት ለማቋቋም የየራሳቸው ሚና ይኖራቸዋል። ማለትም የአንድነት ኀራው መንግሥት ለመመስረት የግድ ከብልጽግና ወይም ከብሔር ተኮር ኀራው ጋር መስማማት ይኖርበታል። ነገር ግን ብሔር ተኮር ኀራውና ብልጽግና ተኮር ኀራው የጥምር መንግሥት ለማቋቋም ከተስማሙ የአንድነት ኀራው ከፍተኛውን መቀመጫ አግኝቶም እያለ ከጨዋታው ውጪ ሊሆን ይችላል። በተለይም ደግሞ የአንድነት ተኮሩና የብሔር ተኮሩ ኀራ ከአጀንዳቸው መራራቅ የተነሳ አብረው ላለመሥራት ከወሰኑ ጥምር መንግሥቱን ለመመስረት ወሳኝ ድርሻ የሚኖረው ከሁሉም ዝቅተኛ መቀመጫ ያሸነፈው ብልጽግና ፓርቲ ይሆናል ማለት ነው።

በአጠቃላይ ከዚህ የምንረዳው በድኅረ ምርጫው ወቅት አስቀድመን ልንመልሳቸው የሚያስቸግሩን የሚከተሉት ከባድ ጥያቄዎች የሚገጥሙን መሆኑን ነው። እነሱም፡-

1. ከፓርቲዎች አብሮ የመሥራት ባሕልና ልምድ አለመኖር ጋር ተያይዞ ሲታይ፣ አንድነት ተኮሩና ብሔር ተኮሩ ጎራ የጥምር መንግሥት ለመመስረት ሊስማሙ የሚችሉበት ዕድል ይኖራል?
2. የአንድነትና የብሔር ተኮር ጎራው ጥምር መንግሥት ለማቋቋም የማይስማሙ ከሆነ፣ አንጋሽ /King Maker/ የሚሆነው ብልጽግና ፓርቲ ከሁለቱ ጎራዎች መካከል ከማንኛው ጋር ለመጣመር ሊመርጥ ይችላል?
3. በሦስቱ ጎራዎች መካከል ያለው አቋም የተራራቀና የተካረረ ከመሆኑ አኳያ፣ አንዱ ጎራ ከሌላው ጎራ ለመጣመር የሚያደርገውን ውሳኔ መራጩ ሕዝብ የማይደግፈው ከሆነ ምን ሊፈጠር ይችላል? ለምሳሌ የብልጽግና ጎራው ከብሔር ተኮር ጎራው ጋር ለመጣመር ቢወስን፣ ብልጽግና ጎራው ለሀገሪቷ አንድነት በጎ አመለካከት ይኖረዋል ብለው በማመን ለብልጽግና ጎራው ድምጻቸውን የሰጡ መራጮች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? እንዲህ ዓይነት ስጋት ካለስ፥ መራጩ ሕዝብ ድምጽ ከመስጠቱ በፊት ማን ከማን ጋር ሊጣመር እንደሚችል አስቀድሞ የማወቅ መብት የለውም ወይ?
4. አንዱ ጎራ ከሌላው ጎራ ጋር ለመጣመር የሚያደርገው ምርጫስ በሀገሪቱ የወደፊት የፖለቲካ ዕጣ ፈንታ ላይ ምን ዓይነት አንድምታ ይኖረዋል?
5. ለመሆኑ እነዚህ ሦስት የፖለቲካ ጎራዎች ከምርጫ ውጤቱ መታወቅ በኋላ አመለካከታቸውን አቻችለው የጥምር መንግሥት ለማቋቋም የሚያስችል ባሕሉና ፍላጎቱ ይኖራቸዋል ወይ?
6. በዚህ ረገድ ስጋት ከኖረስ እነዚህ ሦስት ጎራዎች ጥምር መንግሥት የመፍጠር ድርድር መጀመር ያለባቸው ከምርጫ በፊት ነው ወይስ የምርጫው ውጤት ከታወቀ በኋላ?
7. እነዚህ የፖለቲካ ጎራዎች የጥምር መንግሥት ለማቋቋም ድርድር ሲያደርጉ አንዳቸው ከሌላቸው ለማግኘት የሚጠይቁት የፖለቲካ ጥቅምስ ምን ሊሆን ይገባዋል ወይም ይችላል?
8. እነዚህ ሦስት የፖለቲካ ጎራዎች የጥምር መንግሥት ማቋቋም ሳይችሉ ከቀረስ የሀገሪቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል? የወቅቱ ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ በቀጠለበት ሁኔታ የጋራ የፌደራል መንግሥት ማቋቋም የተሳናቸው፣ ነገር ግን ክልላቸውን በምርጫ ያሸነፉ ፓርቲዎችስ ሕገ መንግሥቱን ተጠቅመው ምን ዓይነት ርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ?

እነዚህ ጥያቄዎች እጅግ ውስብስብና አሁን በሀገሪቱ ከሚታየው የብሔርተኝነትና የጽንፈኝነት የፖለቲካ ባሕል አንጻር በቀላሉ መመለስ የማይችሉ ከባድ ጥያቄዎች ናቸው። ከእነዚህ አስቸጋሪ ጥያቄዎች ውስጥ እዚህ ላይ ቢያንስ በተራ ቁጥር 2 ላይ የተቀመጠውን መሠረታዊ ጥያቄ አንስቶ ለመመለስ መሞከር ተገቢ ይመስለኛል። ማለትም፥ ብልጽግና ፓርቲ አንጋሽ (King Maker) የመሆኑን ዕድል ካገኘ በዚያች ወሳኝ ሰዓት ላይ ከማን ጋር ለመጣመር ይወስናል? የሚለው ጥያቄ እጅግ መሠረታዊ ነው። እዚህ ላይ የራሴን ግምት አስቀምጬ ለማለፍ ልድፈር። በእኔ አመለካከት አሁን ላይ “አቋም የለሽ” ለመሆን የመረጠው የብልጽግና ጎራው፥ እንዲህ ዓይነቱ ወሳኝ ምርጫ ፊቱ ላይ ሲቀመጥ በፍጥነት አቋም ወደ መያዝ የሚሸጋገር መሆኑ አያጠራጥርም። ብልጽግና ፓርቲ ቀዳሚ ዐላማው በሥልጣን ላይ መቀጠል መቻል ቢሆንም ከሁለቱ ጎራዎች አንዱን ለመምረጥ ሲገደድ ግን ከአንድነት ጎራው ይልቅ የብሔር ተኮር ጎራውን መምረጡ አይቀሬ ነው። ምክንያቱም ብልጽግና ፓርቲ በብሔር ፖለቲካ ውስጥ

“ጥርሱንነቅሎ” ያደገና አሁንም እውነተኛ ስሜቱን አድበስብሶ እየሠራ ያለ በመሆኑ ያቺ የቁርጥ ቀን ስትመጣ፣ ከእውነተኛ ወዳጁ ከብሔር ተኮር ኀራው ጋር መጣመርን እንደሚመርጥ መገመት ነቢይ መሆንን አይጠይቅም። ይህ ለእኔ የፖለቲካ “ሀ… ሁ…” ነው።

ስለዚህ የአንድነት ኀራው የአንደኝነት ደረጃውን ይዞም እያለ ከሥልጣን መጋራት የሚገለልበትና በሠላሳ ዓመት ውስጥ ለሦስተኛ ጊዜ ተሸናፊ የሚሆንበት ዕድል ይኖራል ማለት ነው። ይህም ማለት ላለፈው 29 ዓመታት የነበረው ብሔርተኛ ኀይል በሥልጣን ላይ ወደፊትም ይቀጥላል። የዚህ ብሔርተኛ ኀይል የቃል ኪዳን ሰነድ የሆነው ሕገ መንግሥትም ባለበት ሁኔታ በሥራ ላይ የመቀጠል ዕድል ያገኛል። ከዚያ በኋላ የአንድነት ኀይሉ ወደ ሥልጣን የመውጣት ዕድል ሊኖረው ይችላል? የኢትዮጵያ አንድነትና ህልውናስ በዘላቂነት የመቀጠል ዕድል ይኖረዋል? ማንኛውም የኢትዮጵያ አንድነት ህልውና ደጋፊ ነኝ የሚልና በአሁኑ ወቅት የብልጽግና ፓርቲ ዕድሜ እንዲራዘም እየደገፈ ያለ ፓርቲና ዜጋ ለእነዚህ ጥያቄዎች ተገቢ መልስ መስጠት ይኖርበታል። እኔ ይህንን ጥያቄ ለራሴ ጠይቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥቻለሁ። በማንኛውም ሁኔታ የብልጽግና ፓርቲ ዕድሜ እንዲራዘም መደገፍ የ29 ዓመቱን አምባገነንና ብሔር ተኮር ኀይል እንደገና በሥልጣን ላይ የማስቀጠል ውሳኔ ነው። ከዚያም አለፍ ሲል የኢትዮጵያን አንድነትና ህልውና እስከ ወዲያኛው አደጋ ላይ የሚጥልና ልጆቻችንን ሀገር አልባ የሚያደርግ የተሳሳተ ውሳኔ ነው።

ከዚህ የምንረዳው ምርጫው በቅርብ ጊዜ እንዲካሔድ የሚፈልጉ ፓርቲዎችም ሆኑ መራጭ ዜጎች በድኅረ ምርጫው ወቅት የሚከሰተው ሁኔታ ምን ያህል የራሳቸውን ፍላጎትም ሆነ የሀገሪቷን ጥቅም እንደሚያስጠብቅ ለማወቅ ደጋግመው ማሰብ ያለባቸው መሆኑን ነው። እንኳንስ ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ የሆነ ምርጫ ለማካሔድ ዕድሉ በሌለን በአሁኑ ወቅትና፣ በሆነ ተዐምራዊ ምክንያት በአንጻራዊነት ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ለማካሔድ ብንችል እንኳን የድኅረ ምርጫውን ሁኔታ በአግባቡ ይዘን ወደ በጎ አቅጣጫ ለመሻገር የሚያስችል የፖለቲካ ባሕልና የሥርዓት ዝግጅት እንደ ሀገርና ሕዝብ ገና የለንም። ለዚህ ነው፥ ተቻኩለን ወደ ምርጫ ከመግባታችን በፊት በቂ ልምምድና ዝግጅት የምናካሒድበት የሁለት ዓመት የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም እየጠየቅን የምንገኘው።

በአጠቃላይ ምርጫው እንዲራዘምና የእርቅና የአንድነት የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም እየቀረበ ያለውን ጥያቄ ከፓርቲዎች የምርጫ ዝግጅት መኖርና አለመኖር ጋር አያይዞ ማየት ትልቅ ስህተት ነው። በእኛ አመለካከት ምርጫው በቅርብ ጊዜ ይካሔዳል ከተባለ የበለጠ የመዘጋጃ ጊዜ የሚያስፈልጋቸው ምርጫው መካሔድ አለበት በማለት እየተከራከሩ የሚገኙት የብልጽግና ፓርቲና ጥቂት የብሔር ተኮር ፓርቲዎች ናቸው። ምክንያቱም ምርጫው ቢራዘም የብልጽግና ተኮር ኀራው “ከአቋም የለሽነት” ወደ «አቋም ያለው» ኀራ ራሱን ቀይሮ በምርጫው የተሻለ፣ ምናልባትም ወደ አንደኛ ደረጃ አሸናፊነት የሚያሸጋግር ውጤት የማግኘት ዕድል ሊፈጥር ይችላል። ምርጫው ተራዝሞ በሀገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ከሰፈነም የብሔር ተኮር ኀራው ቢያንስ ምርጫ በማይካሔድባቸው 50 የኦሮሚያ የምርጫ ወረዳዎች ተጨማሪ መቀመጫዎችን የማሸነፍ ዕድል ይኖረዋል። ከዚህ አንጻር ምርጫውን የማራዘምና የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄ ከፓርቲ ጥቅም ሳይሆን ከሀገር ጥቅም አንጻር መታየት ስላለበት

ነው እንጂ ምርጫው በዚህ ወቅት መካሔድ ቢችል በአንጻራዊነት ተጠቃሚ የሚሆነው የአንድነት ተኮር ጎራው ነው።

በአጠቃላይ፥ ምርጫው እንዲራዘም የምንጠይቅበት ዋናው ምክንያት ሰላማዊ፣ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ለማካሔድ የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን የሌለ በመሆኑ ምክንያት ቢሆንም፣ አንዳንድ የተሳሳተ ግምት ያላቸው ወገኖች እንደሚያስቡት በሆነ ተዐምራዊ ምክንያት ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ ማካሔድ ቢቻል እንኳን፣ ከምርጫው በኋላ የሚመጣው ውጤት በታሪካችን አይተነው የማናውቀውና በቅጡ ያልተዘጋጀንበት መሆኑን ተገንዝበን ለሽግግር መንግሥት መቋቋም አስፈላጊነት አንድ ተጨማሪና ዋና ምክንያት አድርገን ልናየው ይገባል።

እንዲህ ዓይነቱን ውስብስብ ሁኔታ ግምት ውስጥ ሳናስገባ በተሳሳተ የየራሳችን ግምት፣ በተሳካ የሽግግር ሒደት ውስጥ ሳናልፍ ምርጫው በቅርብ ጊዜ እንዲካሔድ የምናደርግ ከሆነ ግን ሁላችንም ተሸናፊ እንጂ አንዳችንም አሸናፊ መሆን እንደማንችል አስቀድመን መረዳት ይኖርብናል። ይህንን አስቸጋሪ ጊዜ ከአማካይ ደረጃ በታች የሆነ ደካማ የፖለቲካ አመራር ይዘንና ከፋፋይ የምርጫ ሒደት ውስጥ ገብተን ልንወጣው አንችልም። ፍጹም ሰላማዊ ሁኔታ ኖሮን፣ ሁላችንም በአንድነት ቆመን፣ ጠንካራ አመራር ፈጥረንና ሌት ከቀን በሙሉ ትኩረትና ትጋት ሰርተንም የወቅቱን ችግር ልንወጣው ከቻልን ዕድለኞች ነን።

በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት እየቀረበ ያለውን የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ጥያቄ፥ዕዳንና ኀላፊነትን እንደመጋራት ጥያቄ እንጂ ጥቅም የሚያስገኝ ሥልጣንና ሹመትን እንደመጋራት ጥያቄ አድርጎ ገዥው ፓርቲ ባያየውም ጠቃሚ ይሆናል። እኔ ባለኝ መረዳት አብዛኛዎቹ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ጥያቄ በማቅረብ ላይ የምንገኝ የፖለቲካ ሰዎች፣ ጥያቄውን እያቀረብን ያለነው ሀገራችንን ከጥፋት ለመታደግ ካለን ልባዊ ቁጭትና ፍላጎት እንጂ ከዚህ ዕድሜያችን በኋላ የመንግሥት ባለሥልጣን ሆነን ጥሩ መኪና፣ ጥሩ መኖሪያ ቤት፣ ጥሩ ቢሮ እንዲኖረን ፈልገን፣ ወይም ከፍተኛ ደመወዝና አበል እንዲከፈለን፣ ወይም ደግሞ ከእንግዲህ ጉቦ በልተን ለመበልጸግ ወይም ደግሞ ጉልበት ያለው ባለሥልጣን ሆነን "እሰረው፥ ፍታው" ለማለት ፈልገን አይደለም። ፍላጎታችን ይህ ቢሆን ኖሮ አቋራጩ መንገድ ድሮም የኢሕአዴግ፣ አሁንም የብልጽግና ፓርቲ አባል አንድንሆን ስንጠየቅ እሺ ብለን መቀበል ነበር።

እኛ መጋራት የምንፈልገው እንዲህ ዓይነቱን ቁሳዊ ጥቅምና ኀይልን ለመጠቀም የሚያስችል ሥልጣን ሳይሆን የሀገራችንን አጠቃላይ ህልውና በሚመለከቱ ስትራቴጂክ የፖለሲ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣንን ተጋሪ መሆንን ነው። ምናልባት ዕድለኞች ሆነን እነዚህ ስትራቴጂክ ውሳኔዎች ሀገራችንን ከጥፋት በመታደግ ውጤታማ መሆን ከቻሉ፣ ተቃዋሚዎች ልንጋራ የምንችለው አንድ ነገር ቢኖር የታሪክንና የሕዝብን ምስጋና ማግኘት ነው። ገዥው ፓርቲ ይህንን ምስጋና እንዳንጋራው ካልሰሰተ በስተቀር የሽግግር መንግሥቱን ለማቋቋም በሚካሄደው ድርድር ተቃዋሚዎች ቁሳዊ ጥቅምን ለማግኘትና ኀይልን ለመጠቀም ከሚያስችሉ የሥልጣን ቦታዎች ራሳቸውን ለማግለል መስማማት የሚገዳቸው አይመስለኝም። እንዲህ ዓይነቶቹን የሥልጣን ቦታዎች ይጠቅሙኛል ብሎ ካሰበ ገዥው ፓርቲ ይዟቸው ሊቀጥል ይችላል።

እኔ ራሴን ምሳሌ ላድርግና እንኳንስ ከፍተኛ የሚባል ጥቅምና ምንም ዓይነት ደመወዝና አበል ሳይከፈለኝ ሀገሬን በነጻ የማገልገል ዕድል ባገኝ ምንኛ ደስ ባለኝና ራሴን እንደ አንድ ውጤታማ ሰው በቆጠርኩ ነበር። ነገር ግን በእኛ ሀገር የፖለቲካ ባሕል አንድ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ሰው በጠመንጃ አሸንፎ ለሥልጣን ካልበቃ፣ ወይም ለባለ ጠበንጃው ኀይል ራሱን አስገዝቶ ካላደረ በስተቀር የራሱን ነጻ አመለካከት ይዞ አገሩን በፖለቲካ የማገልገል መብትና ዕድል የለውም። ይህ መሆኑ ልብን በሚሰብር መጠን ሀገራችንን ወደኋላ ያስቀረ አሳዛኝ ነባራዊ ሁኔታችን ነው። እኛን በሥልጣን ጥመኝነት ሲከሱ የሚደመጡ ሰዎች ለ29 ዓመት በአፈናና በምርጫ ማጭበርበር ሥልጣንን ርስት አድርገው የኖሩ ሰዎች መሆናቸው ሲታይና፣ የእነዚህን አምባገነኖች ትችት እንደ እውነት ቆጥረው አንዳንድ የኅብረተሰብ ክፍሎች እኛን በሥልጣን ጥመኝነት ሲያሙን ስንሰማ ሁኔታው የበለጠ ልብን የሚሰብር ይሆንብናል።

በአጠቃላይ፥

- የብሔርተኝነትና የጽንፈኝነት የፖለቲካ ባሕል በሀገራችን ነግሦ፥ ሁሉም አሸናፊ እንጂ ተሸናፊ ለመሆን ባልተዘጋጀበት ሁኔታ…
- ክልሎች እስከ አፍንጫቸው ድረስ ታጥቀው ራሳቸውን እንደ ሉዓላዊ መንግሥትና ሀገር እየቆጠሩ ባለበት ሁኔታ…
- ማኅበራዊ ሚዲያን ጨምሮ ልቅ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም በተንሰራፋበትና የፖለቲካ ፓርቲዎችም ጭምር የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ባለቤት ሆነው በሚገኙበት ሁኔታ…
- በኮሮናቫይረስ ምክንያት ሀገሪቷ ከፍተኛ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ውስጥ በገባችበት ሁኔታ…
- ከመቼውም ጊዜ በላይ ሀገራችን ለውጭ ኀይሎች ጣልቃ ገብነትና ጥቃት ተጋላጭ በሆነችበት ሁኔታ…
- ከሁሉም በላይ አንጻራዊ ሰላምና የሕግ የበላይነትን ማስፈን ያልቻለ፣ ከአማካይ ደረጃ በታች የሆነ ደካማ መንግሥት በሥልጣን ላይ ባለበት ሁኔታና፣ እነዚህን መሠረታዊ ሀገራዊ ችግሮቻችንን ሊያቃልል በሚያስችል ስኬታማ የሽግግር ሒደት ውስጥ ሳናልፍ ሀገራዊ ምርጫ ለማካሔድ መጣደፍ፣ በአጭር አገላለጽ ራስን የማጥፋት /Suicidal/ ዓይነት አደገኛና የተሳሳተ ውሳኔ ይሆናል።

በአጠቃላይ፣ ኢትዮጵያዊያን ከእንግዲህ ስኬታማ የሽግግር ሒደት ሳናካሒድ የተለመደው ዓይነት የታይታ ምርጫ በማካሔድ ሀገራዊ ህልውናችንን ማስቀጠል አንችልም። ከእንግዲህ ሀገራዊ ህልውናችን አንጻራዊ ዋስትና አግኝቶ ሊቀጥል የሚችለው ውጤታማ የሆነ የሽግግር ሒደትን ተከትሎ ሊካሔድ በሚችልና በአንጻራዊነት ነጻና ፍትሐዊ በሆነ ምርጫ ብቻ ነው። ይህንን ሒደት ስኬታማ ማድረግ ወይም አለማድረግ ዛሬ ላይ በትውልዱ ፊት የተደቀነ፣ ምናልባትም ዳግም ዕድልና ምርጫ የማይሰጥ ወሳኝና ታሪካዊ ፈተና ሆኗል። የዚህ ትውልድ የወደፊት ውርስ የሚለካውም ይህንን ፈተና በማለፍ ወይም በመውደቅ ይሆናል።

ግንቦት 2012 ዓ.ም.

ልደቱ አያሌው